# የአስር ዓመት
# የልማት ዕቅድ

## 2013 - 2022

ኢትዮጵያ፤ አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# የአስር ዓመት
# የልማት ዕቅድ

## 2013 - 2022

ኢትዮጵያ፤ አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# ማውጫ


ምዕራፍ አንድ፥ ያለፉት ዓመታት አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም እና ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች 1

1.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ 2

1.2 ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች 4

ምዕራፍ ሁለት፥ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ እና የልማት ዕቅዱ አድማስ 7

2.1 ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ 8

2.2 የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ አስፈላጊነት እና ልዩ ባህርያት 14

ምዕራፍ ሶሦት፥ የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች 17

3.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች 18

3.2 የልማት ዕቅዱ ምሰሶዎች እና የትኩረት መስኮች 19

3.3 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ስምምነቶች እና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ትስስር 21

ምዕራፍ አራት፥ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ 23

4.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና የድህነት ቅነሳ 24

4.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ 26

4.3 የፊሲካል ፖሊሲ 28

4.4 የገንዘብ ፖሊሲ እና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት 30

4.5 የልማት ፋይናንስ 31

ምዕራፍ አምስት፥ የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ 34

5.1 የግብርና ልማት 35

5.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት 37

5.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት 38

5.4 የማዕድንና ነዳጅ ልማት 39

5.5 የንግድ ልማት 40

5.7 የቱሪዝም ልማት 41

5.6 የከተማ ልማት 41

ምዕራፍ ስድስት፥ የመሰረተ ልማት ዕቅድ 45
6.1 የትራንስፖርት ልማት 46
6.2 የውኃ ሀብት ልማት 47
6.3 የኢነርጂ ዘርፍ ልማት 49
6.4 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ልማት 50
ምዕራፍ ሰባት፥ የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ 52
7.1 የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት 53
7.2 የማህበራዊ ፍትህ እና ዋስትና ልማት 56
ምዕራፍ ስምንት፥ የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕቅድ 60
ምዕራፍ ዘጠኝ፥ የሠላም ግንባታ እና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዕቅድ 62
ምዕራፍ አስር፥ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዕቅድ 65
ምዕራፍ አስር አንድ፥ የልማት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት 67
11.1 የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች 68
11.2 ክልላዊ እና አካባቢያዊ የተመጣጠነ ልማት እና ተወዳዳሪነት 69
11.3 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት 72

# ምዕራፍ አንድ

## ያለፉት ዓመታት አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም እና ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች

# 1.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

በመጀመሪያው እና በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽ ዕቅድ ትግበራ ዓመታት (2003-2007 እና 2008-2012) ተከታታይነት ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል። ከአቅርቦት አንጻር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ2008 ቋሚ የገበያ ዋጋዎች (constant prices) በአማካይ በየዓመቱ በ9.2 በመቶ በማደግ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 828.2 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1.99 ትሪሊዮን ብር ከፍ ብሏል። ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት በተመሳሳይ ወቅት ታቅዶ ከነበረው የ11 በመቶ አማካይ ዕድገት ግብ አንጻር ሲታይ የ1.8 መቶኛ ነጥብ ጉድለት ያሳያል። የኢኮኖሚ አፈጻጸሙ ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች አንጻር ሲታይም የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በአማካይ በ5.3፣ በ17.2 እና በ9.7 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግበዋል (ሠንጠረዥ 1 እና ሥዕል 1)።

ሠንጠረዥ 1፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች (በመቶኛ)

| | አማካይ | | |
|---|---|---|---|
| | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 |
| ግብርና ዘርፍ | 6.6 | 4.1 | 5.3 |
| የሰብል ምርት | 7.5 | 4.8 | 6.1 |
| የእንስሳት ምርት | 5 | 2.5 | 3.7 |
| ኢንዱስትሪ ዘርፍ | 19.1 | 15.2 | 17.2 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 15.1 | 13 | 14.1 |
| ኮንስትራክሽን | 27.7 | 17.3 | 22.5 |
| አገልግሎት ዘርፍ | 11.1 | 8.2 | 9.7 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 11.7 | 8.9 | 10.3 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 13 | 11.5 | 12.2 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 11.4 | 12.5 | 11.9 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 10.1 | 8.2 | 9.2 |


ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

ለተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የግብርና ዘርፍ በአማካይ የ24 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ከዚህም ውስጥ የዋና ዋና ሰብሎች ንዑስ ዘርፍ 72.7 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይይዛል። የኢንዱስትሪ ዘርፉም በአማካይ የ37.9 በመቶ አስተዋጽዖ ያደረገ ሲሆን ለዚህም የኮንስትራክሽን እና ማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች በቅደም ተከተል የ77.1 በመቶ እና የ22.8 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ይህም ለተመዘገበው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት ዋነኛው ምንጭ የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ መሆኑን ያመላክታል። በሌላ በኩል የአገልግሎት ዘርፉ ለተመዘገበው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት 40.8 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ከዚህም ውስጥ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፍ 37.8 በመቶ ድርሻ ይይዛል። በአጠቃላይ ከአቅርቦት አንጻር የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በዋነኛነት በቅደም ተከተል ከኮንስትራክሽን፣ ከዋና ዋና ሰብሎች እና ከጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፎች የመነጨ መሆኑን የአፈጻጸም መረጃው ያሳያል።

ባለፉት አስር ዓመታት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው በነበረው የገበያ ዋጋ (current prices) በአማካይ በየዓመቱ የ23.9 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 395.9 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት 3.37 ትሪሊዮን ብር ደርሷል(ሠንጠረዥ 1.2)። ከዚህ ውስጥ ጠቅላላ ፍጆታ የ79 በመቶ ድርሻ ሲይዝ የግል ፍጆታ ደግሞ ከሶሥት አራተኛ በላይ አስተዋጽዖ ነበረው።

በሌላ በኩል ጠቅላላ ኢንቨስትመንት፣ የወጪ እና የገቢ ንግድ (አገልግሎትን ጨምሮ) በቅደም ተከተል ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በአማካይ የ35.1 በመቶ፣ የ10.1 በመቶ እና የ25.9 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። በአጠቃላይ የተመዘገበው የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ከፍላጎት አንጻር በቅደም ተከተል ከግል ፍጆታ፣ ከጠቅላላ ኢንቨስትመንት እና ከተጣራ የወጪ ንግድ (አገልግሎትን ጨምሮ) የመነጨ መሆኑን ያሳያል።

ሥዕል 1፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች (በመቶኛ)




ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 31.1 በመቶ በ2009 በጀት ዓመት ወደ 38.4 በመቶ ደርሶ የነበረ ሲሆን በ2010 በጀት ዓመት ግን በወቅቱ በሀገሪቱ በነበረው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ምክንያት የውጭና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት በመቀዛቀዙ እንዲሁም የመንግስት ካፒታል ወጪ እየቀነሰ በመምጣቱ ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ምጣኔ ወደ 34.1 በመቶ ዝቅ ብሎ ነበር። ይሁን እንጂ በ2010 የተካሄደውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ በ2011 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ መሻሻል አሳይቶ ወደ 35.2 በመቶ ከፍ ብሎ ነበር። ሆኖም በ2012 በጀት ዓመት በኮቪድ-19 (Covid-19) ወረርሽኝ ምክንያት ወደ 30.8 በመቶ ዝቅ ብሏል።

ሠንጠረዥ 2፡ የመጨረሻ ጠቀሜታ ወጪዎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጋር በንጽጽር ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | አማካይ | | |
|---|---|---|---|
| | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 |
| ጠቅላላ ፍጆታ | 80.7 | 77.6 | 79 |
| የመንግሥት ፍጆታ | 10.5 | 10.2 | 10.3 |
| የግል ፍጆታ | 70.0 | 67.5 | 68.7 |
| ጠቅላላ ኢንቨስትመንት | 35.0 | 35.2 | 35.1 |
| የወጪ ንግድ (አገልግሎትን ጨምሮ) | 12.5 | 7.8 | 10.1 |
| የገቢ (ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ) | 29.5 | 22.2 | 25.9 |
| የሀብት ክፍተት | (17.1) | (14.5) | (15.8) |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ | 19.3 | 22.4 | 21 |

ምንጭ፡ - የፕላንና ልማት ኮሚሽን

የሀብት ክፍተት (ማለትም በወጪ ንግድና በገቢ ንግድ መካከል ያለው ልዩነት) የመስፋት አዝማሚያ ያሳየ ሲሆን ይህም በአማካይ በየዓመቱ 15.8 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ለዚህም በዋነኛነት የወጪ ንግድ አፈጻጸም እጅግ ደካማ መሆንና የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የማመንጨት አቅም ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም አብዛኛው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በገቢ ንግድ ላይ የተመሠረተ መሆን ከፍተኛውን አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከአጠቃላይ ዓመታዊ ሀገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 17.3 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት 20.9 በመቶ ደርሷል። በተመሳሳይ የነፍስ ወከፍ ገቢ (per capita GDP) በአማካይ የ10.7 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 389 የአሜሪካን ዶላር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1,080 የአሜሪካን ዶላር አድጓል።

ሀገራዊ የድህነት ምጣኔ በ2003 ከነበረበት 29.6 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 23.5 በመቶ ቀንሷል። ይህ ምጣኔ በገጠር በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 30.4 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 25.6 በመቶ የቀነሰ ሲሆን በከተማ ደግሞ ከ25.7 ወደ 14.8 በመቶ ቀንሷል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን በተመለከተ የዜጎች የገቢ አለመመጣጠን አመልካች (Gini coefficient) በ2003 በጀት ዓመት 0.30 የነበረው በ2008 በጀት ዓመት 0.33 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፣ በዚሁ ጊዜ በገጠርና በከተማ በተከታታይ ከ0.37 ወደ 0.38 እና ከ0.27 ወደ 0.28 ከፍ ብሏል።

የሥራ አጥነት ሁኔታን በተመለከተ ሀገር አቀፍ የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በሁለቱም ጾታዎች የመጨመር አዝማሚያ አሳይቷል። የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በ2003 በጀት ዓመት 18 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 18.7 በመቶ ከፍ ብሏል። በ2012 በጀት ዓመት ከ15-29 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የሥራ አጥነት ምጣኔ በአማካይ 25.7 በመቶ ሲሆን ይህም ከሀገር አቀፉ የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ አንጻር ከፍተኛ ጭማሪ ያሳያል። የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በጾታ ስብጥር ሲታይ በ2003 በጀት ዓመት የወንዶች 11.4 በመቶ እና የሴቶች 25.3 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል 12.2 እና 26.1 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል።

## 1.2 ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች

የሀገራችን ኢኮኖሚ ባለፉት ዓመታት ተከታታይነት ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ቢሆንም፣ ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ዜጎችን ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ የተጋረጡ ፈተናዎች ነበሩበት። ኢኮኖሚው ሥብራት እንዲያጋጥመው ካደረጉት ተግዳሮቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፤

- **ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የማስመዝገብ ተግዳሮት፡-** ባለፉት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣትና በዘርፎች መካከል ሊኖር ከሚገባው ትስስር አንጻር ሲታይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ክፍቶች ነበሩበት።

- **የውጭ ክፍያ ሚዛን መዛባት፡-** የአምራች ዘርፉ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ መሆን ካለመቻሉ በተጨማሪ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ መሰል ምርቶች ጋርም ተወዳዳሪ መሆን አልቻለም። በመሆኑም ሀገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ሸቀጦች በአብዛኛው እሴት ያልተጨመረባቸው ውስን የግብርና ምርቶች ናቸው። በተጨማሪም ለሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑ ሸቀጦችን ፍላጎት በሀገር ውስጥ ምርቶች ማሟላት አልተቻለም። በመሆኑም የኢኮኖሚው የገቢ ዕቃዎች ፍላጎት ከዓመት ዓመት እየጨመረ በመሄዱ በወጪና በገቢ ንግድ መካካል ያለው ልዩነት ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል።

- **በቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው ሚዛን መዛባት፡-** ባለፉት ዓመታት ኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ተከስቷል። ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንት ፍላጎቱን በአጠቃላይ ቁጠባው ማርካት ባለመቻሉ የኢንቨስትመነት ቁጠባ ሚዛን መዛነፍ ተስተውሏል።

- **የዋጋ ግሽበትን ማረጋጋት ፈታኝ መሆን፡-** የዋጋ ግሽበት መንስኤዎች በርካታ ቢሆኑም ከፍተኛ እና ተከታታይነት ያለው የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚው ውስጥ መከሰት የማክሮ ኢኮኖሚው አለመረጋጋት ምልክት ተድርጎ ይወሰዳል። ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት በዜጐች ላይ ከሚያስከትለው የኑሮ ውድነት በተጨማሪ ዘላቂ ኢንቨስትመንት እንዳይኖር በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል።

- **የሥራ አጥ ቁጥር መጨመር፡-** የሥራ ስምሪት ሁኔታ የማክሮ ኢኮኖሚውን ጤናማነት ከሚያሳዩ አመልካቾች አንዱ ነው። በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለሀገሪቱ ዜጐች በቂ የሥራ ዕድልም ሆነ አብዛኛው ዜጋ ሊደርስበት የሚችል የኑሮ ደረጃ መፍጠር አልቻለም።

- **አዝጋሚ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እና ደካማ የዘርፎች ትስስር መኖር፡-** ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አዝጋሚ በመሆኑ ኢኮኖሚው ምርታማነቱ ዝቅተኛ ከሆነው የግብርናው ዘርፍ ምርቶች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው የግብርና ምርቶች እንዲሁም ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የመሸጋገር ሂደቱ ደካማ ነበር። የሸቀጦች የወጪ ንግድ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዋነኛነት በግብርና ምርቶች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች በመሸጋገር ቀጣይና አስተማማኝ የወጪ ንግድ ገቢ ማስገኘት ተስኖታል።

- **የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባበስብ አቅም ዝቅተኛ መሆን፡-** ባለፉት ዓመታት ምንም እንኳ የታክስ ገቢ የመሰብሰብ አቅማችን በየዓመቱ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነጻጸር ያለው ድርሻ ግን እየቀነሰ መጥቷል። የመንግሥት ወጪ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና ያስገኘውን ውጤት ለመገምገም፤ ብሎም ትክክለኛውን አቅጣጫ ለማስያዝ የተሰጠው ትኩረትም አነስተኛ ነበር።

- **የፋይናንስ ድርጅቶች ተደራሽነት፡-** የመንግስት ባንኮች መጠነ ሰፊ ብድሮችን ካለበቂ ጥናትና ክትትል ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በረዥም ጊዜ ብድር በመስጠታቸው የንግድ ባንኮችን የብድር ዓይነትና ጥራት አዛብቷል። የመድን ኩባንያዎችም በአብዛኛው በለመዱትና በሚቀላቸው አገልግሎት መታጠራቸውና በሌሎች የመድን አገልግሎቶች ላይ በሰፊው አለመሰማራታቸው የመድን ኢንዱስሪው

እንዳይሻሻል አድርጎታል። በአጠቃላይ የፋይናንስ መሠረተ ልማቱ ባለፉት ዓመታት ዕድገት እያሳየ ቢመጣም ኢኮኖሚው ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የማይመጣጠን እና በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ተደራሽነትም ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል።

- **የማህበራዊ አገልግሎቶችና የመሠረተ ልማት አቅርቦት እጥረትና የጥራት ጉድለት መኖር፡-** ባለፉት ዓመታት በመንገድ፣ በባቡር፣ በኢነርጂ እና በመስኖ ግንባታ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም አቅርቦቱ ካለው የመሠረተ ልማት ፍላጎት አኳያ ሲታይ ከፍተኛ የሆነ ጉድለት ይስተዋልበታል። ከጥራት አንጻርም ሰፊ ጉድለት የሚታይበት ነው። በማህበራዊ አገልግሎቶች ዙሪያ፣ በተለይም በጤናና በትምህርት ዘርፎች ከአገልግሎት ጥራት ጋር የተያያዙ የአፈጻጸም ጉድለቶች ታይተዋል፣ ተደራሽነቱም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ ባሻገር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነት በከተማና በገጠር ሰፊ የሆነ ልዩነት የሚታይበት ሲሆን ይህም ለዜጎች እኩል ዕድል ከመፍጠርና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱን ተጽዕኖ አሳድሯል።

- **አቅም ውስንነትና ብልሹ አሰራር፡-** ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡትን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር በተለያዩ ደረጃዎች የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች ተስተውለዋል። በተለይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት የአቅም ውስንነቶችና የቅንጅት ችግሮች ከመታየታቸውም በላይ የሀብት ብክነት እና ሌብነትም ሰፍኖ የነበረ ሲሆን እነዚህን ሁኔታዎች የሚያስተካክልና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓትም በተገቢ መንገድ የተዘረጋ አልነበረም።

# ምዕራፍ ሁለት

## ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ
## እና የልማት ዕቅዱ አድማስ

# 2.1 ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ያስመዘገበችው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት በዋነኛነት ከጥቅል ፍላጎት (aggregate demand) ዘመም የኢኮኖሚ ስርዓት የመነጨ ነው። ይህም በአብዛኛው ባለፉት ዓመታት በመንግስት ከፍተኛ ወጪ በተስፋፋ የመሠረተ ልማት ዕድገት አማካኝነት የተመዘገበ ነው። ይህ የመንግስት ወጪ በከፍተኛ ብድር እና እርዳታ የተሸፈነ ነው። የመንግስት ወጪ ተግባራዊ የሆነበት አግባብና የተመዘገበው ዕድገት ለዓመታት የዋጋ ግሽበት ፈጥሯል። በተጨማሪም ዕድገቱ ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል በተፈለገው መጠን በቋሚነት አልፈጠረም። በከፍተኛ የብድር ጫና ምክንያት ዕድገቱ ሊቀጥል የማይችልበት ሁኔታ መፈጠሩ ከመንግስት ወጪና ብድር ባሻገር ዕድገቱ የሚቀጥልበት ሌላ አማራጭ የዕድገት ምንጭ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የኢኮኖሚ ዕድገቱን የሚያስቀጥል፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር የሚፈጥር እንዲሁም ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል የሚፈጥር አዲስ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (homegrown economic reform) ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህም የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማዕቀፍ ገበያን መሰረት ያደረገና አቅርቦትን ለማስፋፋት በሚወሰዱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያዎች የሚገለጽ ሲሆን ዋነኛ ዓላማውና ትኩረቱም የግል ክፍለ ኢኮኖሚውን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት በማሳደግ የኢኮኖሚ ዕድገት በሂደት በግሉ ዘርፍ ወደሚመራበት ዕድገት ማሸጋገር ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት በተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ውስጥ ዕድገቱ ወደ ኋላ ሳይመለስ የሚቀጥልና የተንሰራፋውን ሥራ አጥነት የሚቀንስ ይሆናል። እነዚህም ማሻሻያዎች በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በክፍላተ ኢኮኖሚና በመዋቅራዊ ማስተካከያ ተለይተው የሚታዩ ናቸው።

**የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ፡-** ባለፉት ዓመታት የተስተዋለው የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት በቶሎ ተስተካክሎ ኢኮኖሚው ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ በጥብቅ የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት እንዲመራ በመደረግ ላይ ይገኛል። የማክሮ ዘርፉን የሚመለከቱ የኢኮኖሚ ተግባራት በጥብቅ ክትትል እንዲደረግባቸው ተደርጓል። ከዚህ አኳያ በሚከተሉት የማክሮ ኢኮኖሚ የሪፎርም መስኮች በትኩረት በመሰራት ላይ ነው።

- የኢኮኖሚ ዕድገቱን ፈጣን፣ ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ እንዲሆን የተቀናጀ ጥረት በመደረግ ላይ ነው። በቅርብ ዓመታት እየተቀዛቀዘ የመጣውን የኢኮኖሚ ዕድገት ወደ ቀድሞው ፍጥነቱ ለመመለስ የሚያስችሉ ጥረቶች በየዘርፉ በመከናወን ላይ ይገኛሉ። እነዚህም ጥረቶች መላውን ህብረተሰብ፣ ባለሀብቱን፣ የሲቪል ማህበረሰቡን፣ መንግሥትንና የልማት አጋሮቻችንን በሚያሳትፍ መልኩ ተግባራዊ እየተደረጉ ነው። ይህም የሚከናወነው ያለፉትን ዓመታት የልማት ዕቅዶች አፈጻጸም በጥልቅ በመመርመር ከተገኙ መልካም አፈጻጸሞችና እንዲሁም ከተስተዋሉ ድክመቶችና ተግዳሮቶች ልምድ በመቅሰም በህብረተሰቡ ተሳትፎ ተግባራዊ በሚሆን የልማት ዕቅድ አማካኝነት ይሆናል። ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም ከዓይነት አንጻር ያለው አፈጻጸም በዝርዝር ጥናት ተገምግሞ በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የሪፎርም እርምጃዎች ለማመላከት እንደ ግብዓት ይወሰዳል። ይህንንም በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ፈጣን፣ ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ እንዲሆን የተቀናጀ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

- የፊሲካል ፖሊሲን በተመለከተ የተጀመሩ የታክስ፣ የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር እንዲሁም የዕዳ አስተዳደር ማሻሻያዎች፤ የታክስ አሰባሰብ ሥራውን በማዘመን የተሻለ ገቢ መሰብሰብ እንዲቻል ዜጎች በአግባቡ የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስችሉ አዳዲስ አሠራሮች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ። ሆኖም

የሚጠበቅባቸውን ግብር በማይከፈሉት ላይ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ የታክስ ሥርዓቱን ግልጽ በሆነ አሠራር እንዲቃኝ ያደርገዋል። የታክስ ገቢ አሰባሰቡ ዝቅተኛ ቢሆንም ታክስ ከፋዩን በእኩል የማየትና በአግባቡ የማስተናገድ ችግር በጉልህ የሚታይ ነው። በመሆኑም የታክስ አስተዳደሩ ፍትሐዊ፤ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን በርካታ አሠራሮች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን ይህም አበረታች ውጤቶች በማሳየት ላይ ይገኛል።

- ኮንትሮባንድ የመንግሥትን ገቢ ከመጉዳቱም ባሻገር በአምራቹ፣ በንግዱ ማህበረሰብና በሸማቹ ላይ የሚኖረው አሉታዊ ገጽታ የከፋ መሆኑ ግልጽ ነው። የኮንትሮባንድ ንግዱ የሚከናወነው ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያ በምንልካቸው ምርቶች ላይም ነው። በዚህ መሰረት ኮንትሮባንድ ለሀገራችን ወጪ ንግድ መዳከም አንዱ መንስዔ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ መሰረት የኮንትሮባንድ ንግድን ከምንጩ በማድረቅ ሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴን ለማበረታታት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል።

- በተጨማሪም የበጀት አስተዳደርና ቁጥጥር ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል። በዚህ ረገድ ከፍተኛ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት በሕግ የተደነገገው በጀት በትክክል ለተፈለገው ዓላማ መዋሉ የሚረጋገጥበት ተቋማዊ የሆነ አሠራር እንዲኖር ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል። የመንግስት በጀት ኢኮኖሚው ትኩረት በሚሰጣቸው የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ እና ፕሮጀክቶችም ጥልቅ የአዋጭነት ጥናት ላይ ተመስርተው የሚመረጡ እንዲሆን አቅጣጫ ተይዞ በመሰራት ላይ ይገኛል። ፕሮጀክቶቹም በተመደበላቸው በጀትና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቁ የሚያስችል የድጋፍ፣ የክትትል፣ የቁጥጥር እና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ተደርጓል። የሚመደበው የወጪ በጀትም ያስገኘውን ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ አሠራሮች እና በዚህም የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምቶችን ለመውሰድ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

- የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም በመደረግ ላይ ነው። የግሉን ዘርፍ ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ኢኮኖሚውን የገጠሙትን መዋቅራዊ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ቁጠባን በማበረታታት ለግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የፋይናንስ አቅርቦትን ማስፋት እና ፍትሐዊነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህንን ግብ ለማሳካት ገበያን መሰረት ያደረጉ የፋይናንስ ሴክተር ማሻሻያዎች ማድረግ ያስፈልጋል። ገበያ መር የወለድ እና የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ ሥርዓት በሂደት መገንባት፣ የገንዘብ ገበያ አክሲዮን ጥናትን መሰረት በማድረግ ማቋቋምና ማስፋፋት እና የብሔራዊ ባንክ የቁጥጥርና ክትትል አቅምን የማሳደግ ሂደቶች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

- የሀገራችንን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመፈታተን ላይ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማጎልበት የሚያስችሉ በርካታ የፖሊሲ እርምጃዎችን መውሰድ ተጀምሯል። በወጪ ንግድ ዘርፍ የሚታዩ መዋቅራዊ ችግሮችን በመለየት መሠረታዊ መፍትሔ የሚያመጡ የማሻሻያ ሥራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በመሰራት ላይ ይገኛል። በተወሰኑ የግብርና ምርቶች ላይ የተመሰረተውን የወጪ ምርቶችን ስብጥርና መጠን በማሳደግ፣ ከምርታማነትና ከማምረት አቅም ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመቅረፍ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ተጨማሪ እሴት ፈጥሮ እና የወጪ ንግድ ምርቶችን በዓይነትና በመጠን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን የኋሊት ጉዞ በመቀልበስ ዕድገት እንዲያሳይ የሚያስችሉ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በቀጣይ ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

- ሌሎች የውጭ ምንዛሪ ምንጮች ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። መንግሥት ከውጭ ሀዋላ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ የዲያስፖራው ህብረተሰብ ወደ ሀገር ቤት የሚልከው ገንዘብ በባንክ ሥርዓት እንዲያልፍ

ለማድረግ የተለያዩ የማበረታቻ ሥራዎችን በማከናወንና አስፈላጊውንም ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል። የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና እንዲሁም የሥራ ዕድልን ለማስፋት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ፍሰቱ የሚጎለብትበትን መንገድ የማመቻቸት ተግባራት በሰፊው በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

- ከዚህ በተጨማሪም የውጭ ምንዛሪ አስተዳደሩንና ፖሊሲውን በጥናት በመፈተሸ አስፈላጊ ማሻሻያዎች ለማድረግ መሠረታዊ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም የመንግስትን የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም በመገደብ እና የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል። የውጭ ዕዳ ጫናን ለመቀነስ የዕዳ ጫናቸው ከፍተኛ የሆኑ የብድር አይነቶች እንዳይወሰዱ የማድረግና እንዲሁም የተወሰዱ ተመሳሳይ ብድሮችን የዕዳ ክፍያ ጊዜ የማሸጋሸግ ሥራዎች ተከናውነዋል።

**የክፍላተ ኢኮኖሚ ዘርፎች ማሻሻያ፦** ለአንዳንድ የኢኮኖሚ ዘርፎች ልዩ ድጋፍና ትኩረት በመደረግ ላይ ነው። ከዚህ ቀደም በወረቀትና በንግግር ትኩረት የተሰጠው ቢመስልም ግብርና ዘርፉ የሚመጥነውን ትኩረት አላገኘም። ለግብርና ዘርፍ ተዋናዮች የሚሰጠው ድጋፍ በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሻሻል ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ከዚህ አንጻር ለአርሶ አደሩ የሚቀርብ የግብዓት ግብይት የሚቀላጠፍበትና ከመንግስትም የተለየ ድጋፍ እያገኘ ሲሆን ለመስኖ ልማትና እርጥበት መቋጠር የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል። ለግብርና ልማት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠት የግብርና ምርት በአስተማማኝ ሁኔታ በተከታታይ የሚያድግበት መንገድ  በመመቻቸት ላይ ያለ ሲሆን የኢንዱስትሪ፣ የማዕድንና የቱሪዝም ዘርፎችም በተመሳሳይ ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኙ በመደረግ ላይ ነው።

- በግብርና ልማት ዘርፍ፦ በግብርናው ዘርፍ በሚከተሉት ንውስ ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራት ላይ ነው። እነዚህም ዘርፎች አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፤ የግብርና ግብዓትና ፋይናንስ አቅርቦት፣ የእንስሳት እርባታ ምርታማነት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ሁሉም ትኩረት አግኝተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የግብርና አመራረት ዘዴን ማሻሻል፤ ድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ፤ በጥናት ላይ የተመሠረተ የምግብ ዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ እና ዋና ዋና ሰብሎችን በተለይም በአጭር ጊዜ ስንዴን፣ የቢራ ገብስን፣ የምግብ ዘይትንና ጥሬ ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ ናቸው።

- በማዕድን ልማት ዘርፍ፦ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በማሳተፍ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ከዓለም አቀፍ ልምድ በመነሳት ማሻሻያ እየተደረገበት ነው። የማዕድን ሀብታችንን መረጃ የማጠናቀርና ተደራሽ የማድረግ፣ በዚህም የባለሀብቶችን ተሳትፎ የማሳደግ፣ መንግሥትም የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ላይ በሚያደርገው ኢንቨስትመንት ከልማቱ አክሲዮን ድርሻ እንዲኖረው የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው። ይህም መንግሥት በፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የኢንቨስተሩን እምነት ያጎለብታል።

- በቱሪዝም ልማት ዘርፍ፦ ሀገራችን በሌሎች ሀገሮች የማይገኙ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ቢኖሯትም ዕድሉን በአግባቡ ያልተጠቀመችበት መሆኑ ይታወቃል። ይህ ዘርፍ ለውጭ ምንዛሪ ምንጭ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ቱሪስቶችን በተለያየ መልኩ ለመሳብ የሚያስችሉ ተግባራት በሰፊው በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ይህንንም ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም መንግሥት ለግሉ ባለሀብት ተሳትፎ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይ ይገኛል።

- የተቀናጀ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ማረጋገጥ፦ የገቢና ወጪ ዕቃዎችን አጠቃላይ የትራንዚት ጊዜን እና ወጪን በመቀነስ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶቻችን በዓለም አቀፍ ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንዲሁም የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመደገፍ በሚያስችል መልኩ የሀገሪቱን የተቀናጀ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን፣ የገቢና ወጪ ምርቶች የትራንስፖርት ኮሪደሮችን፣ የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ጥራት፣ ቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን የማሳደግ አቅጣጫ ተይዞ በመሰራት ላይ ይገኛል።

- የተወሰኑ ገቢ ምርቶችን የመተካት ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ፦ በዓለም አቀፍ ትስስር በሚመራው ኢኮኖሚ ስትራቴጂያችን በዋናነት ኤክስፖርት መር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየወጣባቸው ያሉ ነገር ግን በትንሽ ጥረት ንጽጽራዊ አቅም ሊፈጠርባቸው የሚችሉ እንደ ምግብ ዘይት፣ ስንዴ እና የግብርና አግሮ ፕሮሰሲንግ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የመተካት ስትራቴጂን በመከተል ሰፊ ሥራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

- የሥራ ፈጠራንና የቢዝነስ ምህዳሩን ማሻሻል፦ የሀገር ውስጥ የሥራ ፈጠራንም ሆነ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት መሠረተ ልማትን ያካተቱና እስካሁን የተሰሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፣ የቢዝነስ ከባቢያዊ ሁኔታን የማሻሻል፣ አላስፈላጊ ቢሮክራሲ የማስወገድ እና የብድር አቅርቦትን የማሻሻል ሪፎርም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል።

- የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ሚና ማሳደግ፦ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረውን ሚና እና ያጋጠሙትን ፈተናዎች በዝርዝር በጥናት በመፈተሽ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡና በተሻለ ሁኔታ እንዲወጣ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ የኢኮኖሚ ሪፎርም እርምጃዎች በቀጣይ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሀገሪቱን የቢዝነስ ከባቢያዊ ሁኔታው በማሻሻል ረገድ የሚሠራው ሥራ ቢሮክራሲያችን በትንሹ የሚያደርገውን መፍጨርጨር ጠልፎ የሚጥል ሳይሆን የሚደግፍና የሚያሳድግ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ይህ ማሻሻያ በፋይናንስ ዘርፉ ከሚደረገው ማሻሻያ ጋር ተመጋግቦ ሀገሪቱ የፈጠራ ሥራዎች መፍለቂያ (start-up nation) እንድትሆን ያደርጋል።

**የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ጉዳዮች ማሻሻያ፦** መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሚና የሚቀጥል ቢሆንም በአፈጻጸም ፖሊሲና ሥልቶች ላይ እንደወቀቱ ሁኔታ ማሻሻያ ማድረግ ይገባል። መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ በተለይ በኢንቨስትመንት ጣልቃ አገባብ የተለየ አሰራር እንዲከተል ማድረግ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ  የገበያ ጉድለት መኖሩ በጠለቀ ጥናት እንዲፈተሽ በማድረግ የገበያ ክፍተት መኖሩ ከተረጋገጠና መንግሥት ጣልቃ መግባት ካለበት የፕሮጀክቱ አዋጭነት በበቂ ሁኔታ እንዲጠና እንዲሁም ጣልቃ ገብቶ ፕሮጀክቱን ለስኬት ለማብቃት በቂ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ አቅምና ሀብት ስለመኖሩ በቅድሚያ የማረጋገጥ አቅጣጫ ተይዞ በመሰራት ላይ ይገኛል። በፕሮጀክት ደረጃም እያለ ይሁን ፕሮጀክቱ ካለቀ በኋላ በቂ አቅም ያለውና ማስቀጠል የሚችል ባለሀብት መኖሩ ሲረጋገጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ ለግሉ ዘርፍ እንዲተላለፍ የሚደረግበት አሰራር ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል።

ከሀገር ውስጥ ባንኮች በሚገኝ ብድር የሚፈጸም ፕሮጀክት ባንኮች ለማበደር አዋጭ መሆኑን ሲያረጋግጡ ተፈጻሚ ይሆናል። መንግሥት ከባንኮች የሚወስደው ብድር የግል ባለሀብቱን የብድር ድርሻ የሚያኮስስ (crowd-ing-out) እንዳይሆን ጥንቃቄ በመወሰድ ላይ ይገኛል።

የመንግስት የመጨረሻው ግብ ጠንካራ የግል ባለሀብት በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲፈጠር ስለሆነ ሂደቱ የግል ባለሀብትን የሚያኮስስ ሳይሆን የሚያጠናክርና የሚያስፋፋ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። የግል ባለሀብቶችን ጨምሮ ሁሉን የልማት ኃይሎች መንግስት መደገፍ ያለበት ለመንግስት ባላቸው ቅርበት ሳይሆን ባላቸው ውጤት ላይ ተመርኩዞ መሆን አለበት። መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ሲል ለፈጠራቸው መንግስታዊ ድርጅቶች ከሌሎች የግል ተመሳሳይ ድርጅቶች የተለየ ድጋፍ የሚያገኙበት አግባብ እንዳይኖር ተደርጓል።

በዚህ መሰረት ሁሉንም የኢኮኖሚ ተዋናዮች በእኩል የሚያሳትፍ፣ ፍትሐዊ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የውድድር ሜዳ መዘርጋት አስፈላጊ ነው። የመጫወቻ ሜዳውን ምቹ የማድረግና ለዚህ የሚያግዙ የፖሊሲና አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ዜጎች በነጻነት ሰርተው የሚኖሩባትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር በርካታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማበረታታት የሚወሰዱት የፖሊሲ እርምጃዎች ሁሉንም የሥራ መስክ የሚመለከቱ በመሆኑ የሚወሰዱ የፖሊሲ ማሻሻያዎች በሙሉ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታቱና የሚደግፉ እንዲሆኑ አቅጣጫ ተይዞ በመሰራት ላይ ይገኛል።

የንግዱ ማኅበረሰብ እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖረው ለማድረግና በነጻ ለመደራጀት እንዲችል፣ ከመደራጀትም በሚገኘው ጥቅም ላይ ትኩረት እንዲሰጥ መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል። ሰፊ የሆነ የውድድር መንፈስ በመፍጠር በማምረትም ሆነ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሁሉ በውድድር ብቻ የጋራ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን ሊቀይር የሚችል ድምፅ ማሰማት የሚችልበት መድረክ ይፈጠራል። የግሉ ዘርፍ የማይተካ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት ሚና ያለው በመሆኑ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ የጎላ ሚና እንዲጫወት መንግስት አድሏዊ ያልሆነና የተመቻቸ የብድር አቅርቦት ስርዓት በመዘርጋት አቅም በፈቀደ መጠንም የሚገኝ የውጭ ምንዛሪን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በማደላደልና ዘርፉም መንግሥት ቅድሚያ በሰጠባቸው የሥራ ዘርፎች ላይ እንዲሠማራ አቅጣጫ በማስያዝ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችል የተሟላና ሁሉን አቀፍ የሆነ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም በሚገነቡ የኢንዱስትሪና የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው አምራች የሚሆኑበትን ስልት ይዘረጋል። በተጨማሪም የሥራ ዕድል መስፋፋትና ሥራ ፈጣሪነት ከኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ጋር የተገናኘና በሂደቱ የሚጎለብት በመሆኑ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የበለጠ እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ መንግስት አስፈላጊውን የፖሊሲና አስተዳደራዊ መዋቅር ለመዘርጋት ጥረት በማድረግ ላይ ነው።

- ግዙፍ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዜሽን ማፋጠን፦ መንግስት ወደ ግል እንዲዛወሩ የወሰነባቸው ድርጅቶች ፕራይቬታይዜሽን ሲጠናቀቅ በኢኮኖሚው ላይ በቅልጥፍናም ሆነ በአገልግሎት ጥራትና ብዛት ላይ የሚመጣው ለውጥ ከፍተኛ በመሆኑ በተፋጠነ ሁኔታ ሂደቱ እንዲጠናቀቅ በትኩረት በመሰራት ላይ ይገኛል።

- የዓለም አቀፍና የአካባቢ የንግድ አካል መሆን፦ ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን የንግድ ድርድር ከጀመረች በኋላ በተለያየ ምክንያት እየተስተጓጎለ አሁን ድርድር ሳታጠናቅቅ ረዥም ዘመን የቆየች ብቸኛ ሀገር የሚል ስም አግኝታለች። ኢኮኖሚያችንን ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ማስተሳሰሩ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ወደብ አልባ በመሆናችን የተለያዩ ወደቦችን በጋራ ለማልማት የጀመርነውን ተግባር አጠናክረን

እንቀጥላለን። በመሆኑም በምሥራቅ የጂቡቲን እና የበርበራን ወደብ፣ በምዕራብ የሱዳንን እንዲሁም በሰሜን የኤርትራን ወደቦች መጠቀም መቻል ወጪ ከመቀነሳችንም ባሻገር አስተማማኝና ዘላቂ አገልግሎት ለማግኘት ይረዳልናል። የትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ አማራጮቻችንን ማስፋት ይቻላል። የአካባቢው የንግድ ቀጠና አባል ለመሆን የፈረምነው ስምምነትም በቁርጠኝነት ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል።

- ነጻ የሰው ኃይል ዝውውርን ማሳለጥ፦ በሀገራችን ያለውን ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በየዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ሥራ ወዳለበት አካባቢ በነጻነት ተዘዋውሮ እና መብቱ ተጠብቆ እንዲሠራ የሚያደርግ አቅጣጫን መከተል ያስፈልጋል።

- የሲቪክ ማህበራት በሀገራችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በተደራጀ መልኩ ተሳታፊ ይሆናሉ። እነዚህ አካላት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል በመቆም የሁለቱን የኢኮኖሚ ተዋናይነት ሚዛን እንዲጠብቅ የሚያደርጉ ናቸው። አንዳንዶች እንደሚፈሩት ነፃ ሃሳብ የሚንሸራሸርበት እውነተኛ ዴሞክራሲ በመገንባት ሚዲያን ጨምሮ የሲቪክ ማህበረሰቡን ሚና ማሳደግ የመንግሥትን ሚና የሚያቀጭጭ ሳይሆን የሚያጎለብትና ውጤታማ እንዲሆን የሚያግዝ ነው። አላማችን የዜጎችን ፖለቲካዊና ሞራላዊ ሥልጣን ያካተተ ፖለቲካል ኢኮኖሚ አተያይ መገንባት ነው። ከዚህ በፊት ያጋጠሙንን ተጽዕኖዎች ለማረምና በሀሳብ ነፃነት መንገስ ምክንያት የሚመጣውን የሕዝብና የሀገር አቅም አሟጦ ለመጠቀም ያግዛል። ሁሉንም ተዋናዮች እንደ አንድ የተዋሀደ አካል (integrated whole) ማየት ያስፈልጋል። ይህም አተያይ ሁሉም ተዋናዮች የሚጫወቱትን ቁልፍ ሚና እና ያለውን ጥልቅ ትርጉም በዋናነት የማየትና የማድነቅ ዕድል ይሠጣል። ይህ ሲሆን ልማት በቁንፅል ቁሳዊ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ዘርፈ ብዙ ነፃነቶችን የሚያሰፋ የተሟላ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ ያግዛል።

- ነባር የልማት አጋሮቻችንን ማበረታታትና ወቅታዊ የልማት ፋይናንስ ምንጮችን ማፈላለግ፦ ሌሎች የሀገራችን የልማት አጋሮች የውጭ ዓለማቀፋዊ/አህጉራዊ ድርጅቶችና መንግሥታት ናቸው። መንግሥት ከልማት አጋሮቹ ጋር በመተማመን በሚፈጥረው መድረክ የልማት ፋይናንስ ለማግኘት የሚያደርገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ የአፈጻጸም አቅም ለማጎልበት የሚረዱ የቴክኒክና የአሰራር ዕገዛዎችን ያበረታታል፤ በአግባቡም ተጠያቂነትና ግልጽነት በሰፈነበት መንገድ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል። የግሉን ዘርፍ ለማጎልበትም የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የልማት አጋርነት ሥርዓትን እንዲሁም በሙሉም ሆነ በከፊል ወደ ግሉ ዘርፍ የሚዞሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አተገባበር የልማት አጋሮቹ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የልማት አጋሮቻችን ከልማት እርዳታ ባሻገር የውጭ ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ በማድረግ በትብብር እንዲሰሩ ማበረታታት ይጠበቃል። በአሁኑ ወቅት የሚስተዋለው ዓለም አቀፍ የልማት ፋይናንስ ፍሰት ነባሩን ሂደት የሚከተል አለመሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። ቀደም ሲል የታዳጊ ሀገሮች የልማት ፋይናንስ ምንጭ የነበሩት ባለብዙ ወገን መድረኮች እና ሁለትዮሽ የፋይናንስ ምንጮች አቅርቦት እየቀነሰ በአዳዲስ ሁለትዮሽ ሀገሮችና የግል በጎ አድራጊ (philanthropic) ድርጅቶችና ግለሰቦች ምንጭ እየተተካ መምጣቱ ይስተዋላል። ይህን ሁኔታም በመገንዘብ ሀገራችን ከወቅታዊ የልማት ፋይናንስ አቅርቦት ይበልጥ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማድረግ በመሰራት ላይ ይገኛል።

# 2.2 የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ አስፈላጊነት እና ልዩ ባህርያት

የአንድ ሀገር የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ሚና በዋናነት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በየምዕራፉ በሚኖሩ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች አማካኝነት የሚተገበሩ መሠረታዊ ዓላማዎችን፣ ግቦችን እና የማስፈፀሚያ ሥልቶችን በማስቀመጥ የዕቅዶችን ተፈፃሚነት በተደራጀ እና በተቀናጀ መንገድ ለመምራትና ለመከታተል የሚያስችል ነው። ይህም ማለት የልማት ዕቅዱ ለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራተጂክ አቅጣጫዎችንና ዓላማዎችን በማስቀመጥ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትንና ልማትን በረጅም ጊዜ ዕቅድ በመምራት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የማምጣት ዓላማን ለማሳካት ብሎም ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በግልጽ በማስቀመጥ ውጤታማና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና የጋራ ብልጽግናን ለማስፈን ያስችላል።

ከፍጹም ድህነት ወደ የማይቀለበስ ብልጽግና የሚደረግ ሽግግር የአንድና ከዚያ በላይ ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል። በዚህም መሠረት በአንድ ትውልድ ዕድሜ ብልጽግናን በርዕይ ደረጃ ማመላከት የሚቻል ሲሆን ስኬቱ በትክክለኛ ጎዳና መሆኑን ለማመላከት በቂ ጊዜ ያስፈልገዋል። በተለይም በልማት ሂደት ውስጥ የዓመት፣ የአምስት ዓመት እና የአስር ወይም አስር አምሥት ዓመታት ዕቅዶች ሊፈጸሙ እንደታሰቡት ጉዳዮች ሁኔታ የተለያዩ ናቸው። በዝቅተኛ የድህነት ምጣኔ፣ በመካከለኛ ወይም ከፍተኛ ደረጃ የሚገለጽ የገቢ አቅም፣ ከፍተኛ የሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ፣ ዘላቂ የኢኮኖሚ መዋቅር፣ ዘላቂ የከተማ ልማት፣ የኑሮ ደረጃ መሻሻል፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና በመሳሰሉ ጉዳዮች የሚገለጹ ጥቅል የልማት ግቦች በአጭር ጊዜ የሚረጋገጡ ስላልሆኑ ከአስር ዓመት በማያንስ የጊዜ ሰሌዳ ይመላከታሉ። የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችም በረጅም ጊዜ ዕቅዱ የተመላከቱትን ግቦች ለማሳካት የሚተገበሩ ዝርዝር ዕቅዶች ናቸው።

የልማት ሂደትን የሀብት መፍጠሪያ አቅም መገንባት፣ ሀብት መፍጠር እና ሀብት በፍትሐዊነት መከፋፈሉን ማረጋገጥ በሚሉ ሦስት ደረጃዎች መከፋፈል ይቻላል። የሀብት መፍጠሪያ አቅም በኢንቨስትመንት ይረጋገጣል፤ ሀብት በኢኮኖሚ ዕድገት ይፈጠራል፤ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በፖሊሲ እውን ይሆናል። የእነዚህ ሂደቶች ትግበራም የተለያየ ጊዜ ይወስዳል። በአንድ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ስለ ኢንቨስትመንትና ተያያዥ ጉዳዮች፣ ስለዝርዝር የዘርፎች ተግባር እና በፖሊሲ ደረጃም ስለ ጥቅል ኢኮኖሚ መረጋጋት ሊታቀድ ይችላል። በአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ስለ መሠረተ ልማቶች ግንባታና ስለ ፈጣን የመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊታቀድ ይችላል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ ዘላቂ ልማት እና ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥራት ያለው ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ከአስር ዓመት ባነሰ የጊዜ ሰሌዳ ማቀድ አይቻልም። ከዚህ አንጻር አስርና ከዚያ በላይ ዓመታት የሚወስዱ የረጅም ዘመን ዕቅዶች አመላካችና አቅጣጫ ጠቋሚ ሲሆኑ የአምስት ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅዶች በረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ የተመላከቱ ዋና ዋና ግቦችን ለማስፈጸም የሚታቀዱ ዝርዝር ጉዳዮች ይሆናሉ። በአስር ዓመት ሊደረስባቸው የሚገባቸውንና የሚችሉትን ግቦች ግምት ውስጥ ያላስገባ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ በብዙ መልኩ ግቡን የሚያሳካ ዕቅድ ሊሆን አይችልም።

ይህን ጉዳይ በምሣሌ ለማስረዳት የቡና ልማት ችግኝ ከማፍላት እስከ ምርት ባለው ሂደት የአምሥት ዓመት ጊዜ ሊያስፈልገው ይችላል። በአንድ ዓመት ውስጥ ሊታቀድ የሚችለው ችግኝ አፍልቶ ከመትከልና ችግኙ መጽደቁን ከማረጋገጥ አይዘልም። ቡና በመትከል ተጠቃሚነትን ግብ ላደረገ ገበሬ ትልቁ ዕቅድ ግን የአምሥት ዓመት ዕቅድ ይሆናል። ገበሬው ስለሚኖረው የቡና ምርት መጠን፣ የቡናው ምርት ተሽጦ ስለሚገኘው ገቢ፣ በገቢው ስለሚሟሉ

ፍላጎቶች ከአምሥት ዓመታት ባነሱ ጊዜያት እንደሚሟሉ አድርጎ ማቀድ አይቻለውም። ይልቁንም እነዚህ ግቦች በአምሥት ዓመት ዕቅድ ከተመላከቱ በኋላ ዝርዝር አፈጻጸሞች የአምሥት ዓመት ግቦችን መሠረት አድርገው በአንድ ዓመት ተመጥነው ይታቀዳሉ።

## የአሰር ዓመት ዕቅዱ ልዩ መለያ ባህሪት፣

- የልማት ዕቅድ ዝግጅቱ የዘርፎችን ትስስር ያማከለ እንዲሆን መደረጉ፦ የአሰር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አንዱ መለያ የዘርፎችን ትስስር ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ነው። የዘመናዊ ግብርና፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪንና የማዕድን ዘርፎችን አንዱ ለሌላው ግብዓትና ፍላጎት በመሆን እንዲደጋገፉ፣ ንግድና የሎጅስቲክስ እንዲሁም አገልግሎት የአምራች ዘርፎችን በማሳለጥ ምርትን ከገበያ ጋር የማገናኘት ሚና እንዲወጡ በልማት ዕቅዱ ዝግጅት ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል። በተመሳሳይ መሠረተ ልማት (መንገድ፣ ኢነርጂ፣ መስኖ፣ ሌሎች የትራንስፖርት መንገዶች፣ መገናኛዎች) ለሌሎች ዘርፎች መልማት መሠረት እንዲሆኑ እንዲሁም የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ የምርታማነት ወሳኝ ማረጋገጫዎች በመሆናቸው የሁሉንም ዘርፎች ልማት በሚያሳልጡበት አግባብ ታቅዷል።

- የዘርፎች ትስስር ወሳኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ምርታማነት፣ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም፣ ሌሎች ዘርፎችን የማነቃቃት አቅም ያላቸውና ለበርካታ ዜጎች የኑሮ ደረጃ መሻሻል መሠረት የሚሆኑ ዘርፎች በቀጣይ አስር ዓመት የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ዘመናዊ ግብርና፣ የአምራች ኢንዱስትሪ እና የማዕድን ዘርፎች በአምራች ዘርፍነት የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን እነዚህ ዘርፎችም በግብዓትና በፍላጎት የእርስ በእርስና ውስጣዊ ትስስር በሚደጋገፉበት አኳያ ታቅዷል። በተጨማሪም የልማት ዕቅዱ ኢትዮጵያ ባላት የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦች ምክንያት የቱሪዝም ዘርፍ ለአገልግሎት ዘርፎች መጠናከር እንዲሁም ለአምራች ዘርፎችና የመሠረተ ልማት ግንባታ ወሳኝ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በማስገኘት ሊጫወት ከሚችለውን ሚና ከግምት ያስገባ እንዲሆን ተደርጓል። እነዚህን ዘርፎች ለማልማትም መሠረተ ልማት ቁልፍ ሚና ስለሚኖራቸው የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በአብዛኛው ከዘርፎች ትስስር ጋር የተቆራኘ ነው። በተጨማሪም የልማት ዕቅዶች ተፈጻሚ የሚደረጉት በዘርፍ ተቋማት እንደመሆኑ ተቋማቱ ስለዘርፎች የመልማት አቅም፣ መሠረታዊ ክፍተቶችና እና የመፍትሄ አቅጣጫ የተሻለ ግንዛቤ አላቸው። በመሆኑም የልማት ዕቅድ ከላይ ወደታች የሚወርድ ሳይሆን በዘርፎች ተሳትፎ እንዲታቀድ ተደርጓል።

- አሳታፊና ሀገራዊ የልማት ማዕከላትን የለየ መሆኑ፦ በሀገሪቱ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የሚደረጉ የልማት ዕቅዶች ከሀገራዊ የልማት ዕቅድ ጋር የሚያስተሳስር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት መኖር ለልማት ዕቅዱ ውጤታማነት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም በክልሎች እና ከክልሎች በታች ባሉ የመንግሥት አካላት የልማት ዕቅድን የሚመራ አቅም እና በቂ ፋይናንስ እንዲኖር ማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎችን እምቅ አቅም በመለየት እነዚህን አቅሞች መሰረት ያደረገ የተደራጀ የኢንቨስትመንት ፍሠት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አካባቢዎች የተፈጥሮ፣ የሰው ኃይል እና  አቅሞችን በአግባቡ በመጠቀም ለልማት ዕቅዱ መሳካት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በዚህም መሠረት በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ሀገራዊ የልማት ዕቅድና የክልል መንግስታት የልማት ዕቅዶች ያላቸውን የመልማት እምቅ አቅም በመቃኘት እና በማጣጣም እንዲሁም ሀገራዊ የልማት ማዕከላትን በመለየት የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ከተመረጡ የልማት ማዕከላት ጋር የተቀናጁበትን አግባብ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ተደርጓል።

- የሥርዓታት ድክመትን እንደ ዋና ተግዳሮት በመውሰድ ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ የሚደረግበት አቅጣጫ መያዙ፦ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመዋቅራዊ ለውጥ ረገድ ለተስተዋለው ዝቅተኛ አፈጻጸም አንዱና ዋናው ምክንያት የሥርዓታት ድክመት እንደሆነ ታምኖበታል። የተቋማት ዝቅተኛ የማስፈጸም አቅም፣ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መላላት፣ የተጠያቂነት አለመስፈን፣ በግሉ ዘርፍ ያልተገቡ ባሕርያት መታየትና ከመንግሥት ተቋማት ብልሹ አሠራሮች ጋር መቆራኘት እንዲሁም ከሀገራዊ የጋራ ስምምነቶች ይልቅ የተናጠል ፍላጎቶች ልቀው መገኘትና ለሠላም መደፍረስ መንስኤ መሆን የሥርዓታት ድክመት መገለጫ ሆነዋል። የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እነዚህን ክፍተቶች ከግምት በማስገባት የሥርዓታት መሻሻልና ለውጥ የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን የለየ ሲሆን በዚህም የተሻሉ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፎች ተግባር ላይ  እንደሚውሉ ታሳቢ አድርጓል።

- ሀገር በቀል የኢኮኖሚ መሻሻያ ተነድፎ ወደ ተግባር መገባቱ እና ለዚህ ዕቅድ እንደመነሻ መወሰዱ፦ የሥርዓታት ጉድለትን ለማቃናት እንዲሁም የኢኮኖሚ መዛባትን ለማስተካከል የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተነድፎ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህም በማክሮ ኢኮኖሚ መስክ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን የማጠናከር፣ የውጭ ምንዛሪ ክምችትን የማሳደግ፣ የዋጋ ግሽበትን የመቆጣጠር፣ የፋይናንስ ዘርፉን የማዘመን እና አካታችነቱን የማረጋገጥ እንዲሁም ዋና ዋና የልማት ምንጭ የሆኑትን እና አዳዲስ የዕድገት ምንጭ ሆነው የተለዩትን ዘርፎች ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ በመሆኑ አሁን ያሉትን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶች በመቅረፍ ለቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት መደላድል ይሆናል። በመሆኑም በኢኮኖሚ ማሻሻያው የተመላከቱ የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ የትኩረት መስኮችና የመዋቅራዊ ማሻሻያ ሥልቶች ለአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እንደመነሻም ተወስደዋል።

- የግሉ ዘርፍ ዋና የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተር መሆኑን በመቀበል የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ትብብር የሚጠናከር መሆኑ፦ በአለፉት አስር አምሥት ዓመታት በታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የመንግሥት ሚና ከፍተኛ ነበር። የመንግሥት የልማት ስኬቶች በአብዛኛው በኢኮኖሚና ማሕበራዊ መሠረተ ልማቶች ላይ የተንጸባረቁ ሲሆኑ ዋና የዕድገት ምንጮቹም እነዚህ ፍላጎትን የሚያበረታቱ ዘርፎች ነበሩ። ጥራት ያለውና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት መረጋገጥ የሚችለው በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሲሆን በቀጣዮቹ አስር የልማት ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የግሉ ዘርፍ በተለይም የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ በወሳኝ አምራች ዘርፎች ላይ እንደሚሰማራ ትልቅ ተስፋ ተጥሏል። ይህ ዕቅድ ዳር እንዲደርስም የግሉ ዘርፍ የመንግሥትን የልማት አቅጣጫ እንዲረዳና በምክክር ሲዳብርም እንዲቀበለው እና መንግሥትም የግሉ ዘርፍ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በተቀላጠፈ መንገድ እንዲፈታ የማድረግ ዓላማ ያለው በልማት ሂደት የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ እውነተኛ ትብብር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ
## መነሻዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

# 3.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች

የልማት ዕቅዱ የተሳካ ይሆን ዘንድ ወደፊት ሊደረስበት የሚታሰበው ደረጃ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ እና ወደፊት ሊከሠቱ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችን እና ተግዳሮቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። ከዚህ አንጻር የሀገራችን ርዕይ፤ እየተተገበሩ ያሉ እና በቀጣይ ተግባራዊ የሚሆኑ ሀገራዊ እና የዘርፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤ በቅርቡ እየተካሄደ ያለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም፤ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችና በትግበራ ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች፤ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም ከባቢያዊ እና ዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎችና ለውጦች በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊያሳድሩ የሚችሉት አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ በልማት ዕቅዱ እንደ መነሻ ተወስደዋል። ዋና ዋና የዕቅዱ መነሻዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 3.1.1 ሀገራዊ የረጅም ጊዜ የልማት ርዕይ

የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ መነሻ ያደረገው ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ማድረግ ነው። በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚረጋገጥ ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ አንድ የብልጽግና ምንጭ እንጂ በራሱ የብልጽግና መለኪያ አይሆንም። ብልጽግና ቁሳዊ፣ ሰብዓዊ እና በማህበራዊና መልካም እሴቶች የሚገለጹ የማይዳሰሱ ባህሎቻችንንና ሀብቶቻችንን በማነጽ በምንፈጥራቸው አቅሞች፤ አቅሞቹም በሚፈጥሯቸው ጥሪቶችና የተገነቡ ሥርዓታት፤ ጥሪቶችና ሥርዓታት በሚያሟሏቸው የሰው ልጅ ፍላጎቶችና መሻቶች እንዲሁም እነዚህን ፍላጎቶችና መሻቶች በማሟላት ረገድ የሚገለጽ የተድላ፣ የዕርካታና የምልዑነት ደረጃ ነው። በዚህም መሠረት ብልጽግና፦

1. ዜጎች ፍላጎቶታቸውንና መሻቶቻቸውን የሚያሟሉባቸው በየደረጃው በፍትሐዊነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችሉ የገቢ አቅምና ጥሪቶች እንዲሁም እነዚህን ጸጋዎች ለመፍጠር በሚያግዙ ቁሳዊ፣ ሰብዓዊና ተቋማዊ አቅሞች፤
2. ዜጎች ያላቸውን እምቅ ችሎታ በሚገባ ተጠቅመው ጸጋዎችን በፍትሐዊነት መፍጠርና መቋደስ በሚያስችሉ እንደ ትምህርት፣ ጤና እና ሌሎች አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነት፤
3. ሁሉም ዜጎች የኢኮኖሚ አቅማቸው ፈቀደም አልፈቀደም ለመኖር መሠረታዊ የሆኑትን እንደ ተመጣጣኝ ምግብ፣ መጠለያ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሀ፣ መሠረታዊ የጤናና ትምህርት አገልግሎቶች ተጠቃሚነት እና
4. ዜጎች የተለያዩ ማህበራዊ ማንነቶች ሳይገድቧቸው በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያለምንም ተጽዕኖ በእኩል ተሳታፊነታቸው በጋራ በሚገነቡ አዎንታዊ ሥርዓታት ይገለጻል።

ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት የሚከናወኑ የልማት ተግባራትና የሚመዘገቡ የልማት ውጤቶች ወደዚህ ሀገራዊ ርዕይ በአስተማማኝ ደረጃ የሚያደርሱን መሆን አለባቸው። ከዚህ አኳያ የማህበረሰባችንን ብልጽግና ለማረጋገጥ በአንድ በኩል አብዛኛው ማሕበረሰባችን ከራሱ መልካም እሴቶች በመነሳት የልማት ጥግ አድርጎ የሚወስዳቸውን ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት በየደረጃው በተደረሰባቸው አቅሞች ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በማስፈን፣ በሌላ በኩል ሌላው ዓለም የደረሰባቸውን የብልጽግና ጫፎች ከራሳችን አድማስ ባሻገር በማየትና ሌሎች የሄዱባቸውን ጠመዝማዛ መንገዶች በማረም እኩል የዓለም ዜጋ የሚያደርገንን ፍኖት በመቀየስ አማካይ ገቢን ብቻ ሳይሆን ብልጽግናን እናቅዳለን።

በጥቅሉ ብልጽግና የሰዎችን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችሉ አቅሞች፣ በውጤቱ በታዩ የኑሮ ደረጃ መሻሻሎች እና በሰዎች የእርካታ ደረጃ አመለካከት ሊገለጽ ይችላል። ከዚህ አንጻር የነፍስ ወከፍ ገቢና የፍትሐዊነት የሀብት ክፍፍል ደረጃ፣ አንድ ዜጋ በሕይወት የሚቆይበት አማካይ ዕድሜ እና በተለያዩ የኑሮ ደረጃ መስፈርቶች፣ የፍትሕና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የነጻነት ጉዳዮች ዜጎች ያላቸው የእርካታ ደረጃ መለኪያነት ይወሰዳሉ። በዚህም መሠረት ለብልጽግና ደረጃ መለኪያነት ሶሥት ዋና ዋና አመልካቾች የተመረጡ ሲሆን እነዚህም የሰብዓዊ ልማት አመልካች (Human Development Index)፤ የፊርጀ ብዙ ድህነት አመልካች (Multidimensional Poverty Index) እና ዜጎች በኑሮአቸው ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ (Perception of Wellbeing) ናቸው።

### 3.1.2 የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ዋና ዋና ዓላማዎች የታለመውን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ሃገር የመፍጠር ሀገራዊ የረጅም ግዜ የልማት ርዕይ ለማሳካት ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል፤


1. የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ገበያ-መር የኢኮኖሚ ሥርዓት (pragmatic market-based economic system) በመከተል የግል ዘርፉን ጉልህ ሚናና ተሳትፎ በማሳደግ የበለጸገች ሀገር መገንባት፤
2. የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣንና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብና ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፤
3. አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርታማነትን፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማጎልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ (structural economic transformation) ማረጋገጥ፤
4. የማህበራዊና የመሠረተ ልማት ጥራትንና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
5. ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የሕዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት በማጎልበትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ እና
6. ሰላምና ፍትሕ የሚያረጋግጡ ጠንካራ ሥርዓታት በመገንባትና የሕግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማስከበር የዜጎችን ደህንነት ማረጋገጥ።

## 3.2 የልማት ዕቅዱ ምሰሶዎች እና የትኩረት መስኮች

የልማት ዕቅዱ ዝርዝር ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች (strategic pillars) ያሉት ሲሆን እነዚህም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን እና የጋራ ብልጽግናን ማረጋጋጥ፣ የኢኮኖሚ ምርታማነትን እና ተወዳዳሪነትን ማረጋጋጥ፣ የቴክኖሎጂ አቅምን እና ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት፣ ዘላቂ የዕድገት እና የልማት ፋይናንስን ማረጋገጥ፣ የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነት ማረጋገጥ፣ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፣ የሥርዓታት ለውጥን ማረጋገጥ፣ የልማት ተጠቃሚነትን እና ማህበራዊ አካታችነትን ማረጋገጥ፣ የፍትሕ ተደራሽነትን እና ውጤታማ መልካም አስተዳደርን ማስፈን እና ዘላቂ የሰላም ግንባታና ጠንካራ ቀጠናዊ ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ማረጋገጥ ናቸው።

የሚታቀዱ ሁሉም የልማት ዕቅዶች ለሀገሪቱ ርዕይ መሳካት የማይተካ ሚና አላቸው። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ቅድሚያ ሰጥታ (priority focus areas) ልትፈታቸው ካሰበቻቸው ማነቆዎች ውስጥ ዘርፎች ባላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚና፣ በትንሽ ጥረት ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ባላቸው አቅም፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ባላቸው ትስስርና በእነዚህ ዘርፎች ላይ በሚያመጡት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ፣ ሀገሪቷን ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ ባላቸው አቅም እንዲሁም ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ ባላቸው የጎላ ድርሻ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሥዕል 2 ፡ የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ምሰሶዎች እና የትኩረት መስኮች



# 3.3 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ስምምነቶች እና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ትስስር


የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 እ.ኤ.አ. በመስከረም 2015 የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት መሪዎች በኒውዮርክ ባደረጉት ስብሰባ ፀድቆ ይፋ የሆነና በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ቋት የተተካ ነው። ይህ የልማት አጀንዳ የማይነጣጠሉና ሁሉን አቀፍ (Universal) ባህሪያት ያሏቸው 17 ግቦችን፣ 169 ኢላማዎችና 230 አመልካቾችን ያካተተ ነው። የዘላቂ ልማት ግቦችን ከመፈፀምና ከማስፈፀም አኳያ በዓለም አቀፍ ደረጃ አስገዳጅ የህግ ማዕቀፍ ባይኖርም የዓለም ሀገራት መሪዎች የጋራ የቃል-ኪዳን ሰነድ ሆኖዋል። ይህም የየሀገራቱን ልማት የበለጠ ለማፋጠን እና ስኬታማ ለማድረግ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል። ሀገራችን ኢትዮጵያም ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት በአህጉራዊ ግብዓትነት የተወሰደውን እና “Common African Position on Post 2015 Development Agenda” የተሰኘውን የአፍሪካ የጋራ አቋም ሰነድ ለማዘጋጀት የከፍተኛ ኮሚቴ አባል ሆነው እንዲሠሩ ከተመረጡ 10 የአፍሪካ ሀገራት መካከል የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በመወከል ተመርጣ አስተዋጽዖ አድርጋለች።

የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የማስተሳሰር ሥራ ተሰርቷል። የዘላቂ ልማት ግቦች ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዝግጅት እንደ አንድ መነሻነት የተወሰዱ ሲሆን በልዩ የትኩረት መስኮች፣ በመሠረታዊ አቅጣጫዎች፣ በማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ፣ በኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ዕቅድ፣ በማስፈፀሚያ ፋይናንስ ዕቅድ፣ በመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ፣ በሰው ኃብት ልማትና በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዕቅድ፣ በልማታዊ መልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅድ እንዲሁም በባለ ብዙ ዘርፎች ዕቅድ እንደየአግባቡ የማስተሳሰር ሥራዎች ተሰርቷል። በተጨማሪም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063ን እንዲካተት ተደርጓል። ዕቅዱን በሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ቀጥሎም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማፀደቅ የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የህግ አስገዳጅነት እንዲኖራቸው ተደርጎ ባለፉት አምስት ዓመታት ሲተገበር ቆይቷል።

የዘላቂ የልማት ግቦች በቀሪዎቹ አስር ዓመታት ተግባራዊ የሚሆኑ በመሆናቸው በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ እደተደረገው ሁሉ ከአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ጋር ሙሉ በሙሉ ለማስተሳሰር እና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች አኳያ መተግበር ያለባቸውን ተግባራት በመለየት ግቦቹን ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ለማድረግ የዘላቂ የልማት ግቦች ትግበራ የፋይናንስ ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል። ጥናቱን በግብዓትነት በመጠቀም ሁሉንም የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገሪቱ የረጅም ጊዜ ርዕይ፣ከልማት ዕቅዱ ዓላማዎችና ምስሶዎች ጋር በግብ ደረጃ እንዲተሳሰሩ ተደርጓል (ሥዕል 3)። በተጨማሪም በክትትልና ግምገማ ማትሪክስ ሰነድ ውስጥ በኢላማና አመላካች ደረጃ ሙሉ በሙሉ እንዲተሳሰሩ ተደርጓል።

በሌላ በኩል በዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ወቅትና ድርድሮች ላይ የአፍሪካ ህብረት 2063 አጀንዳ ተቀባይነት እንዲኖረው ተፅዕኖ መፍጠር ችላለች። በዚህም 17ቱ የዘላቂ ልማት ግቦች ከአፍሪካ አጀንዳ 2063 ውስጥ ካሉ 20 ግቦች ጋር ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እንዲካተቱ ተደርጓል። በመሆኑም የዘላቂ የልማት ግቦችን ከአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ጋር እንዲተሳሰሩ ሲደረግ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063ም እንደተሳሰረ ታይቷል።

ሥዕል 3፡ የዘላቂ ልማት ግቦች ከአስር ዓመቱ ዕቅድ ምሰሶዎች ጋር ያላቸው ትስስር



# ምዕራፍ አራት

## የአስር ዓመቱ
## የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ

የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ሀገራዊ ርዕይን ለማሳካት ወሳኝ በሆኑት የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በዚህ መሠረት የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፣ ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚውን የዕድገት ቀጣይነትና ዘላቂነት ማረጋገጥ እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ናቸው።

## 4.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና የድህነት ቅነሳ

የድህነት ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 19 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7 በመቶ ለመቀነስ የተገነቡ እና ሊገነቡ የታሰቡ ጥቅል ሀገራዊ አቅሞችን፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊፈጠር የሚችለውን የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲሁም በእያንዳንዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ያሉ አቅሞችንና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ዝቅተኛ የምርታማነት መነሻዎችን ታሳቢ በማድረግ ኢኮኖሚው ከ2013 እስከ 2022 ባሉት አስር ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ በ10 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል።

በተጨማሪም በቀጣዩ የልማት ዕቅድ ዘመን የሀገሪቱን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማረጋገጥ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሪነት ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መሪነት በማሸጋገር፣ የሀገሪቱን አለማቀፍ የገበያ ተወዳዳሪነት በማሳደግና በወጪ ንግድ ገቢ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ እንዲሁም የልማት ፋይናንስ ምንጭ በአብዛኛው የግሉ ዘርፍ እንዲሆን በማድረግ የልማት ፋይናንስን ዘላቂነት ብሎም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ታሳቢ ተደርጓል።

የቁሳዊና ሰብዓዊ ካፒታል ክምችትን ከማሳደግ ጎን ለጎን አጠቃቀማቸውን ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ዘርፎች በማሸጋገርና ቅልጥፍናንና ምርታማነትን ማዕከል ያደረገ ስልትን ታሳቢ በማድረግ የካፒታል ክምችት (capital accumilation) እና አጠቃላይ ምርታማነት (total factor productivity) ለዕድገቱ የሚኖራቸው አስተዋጽዖ በቅደም ተከተል 55 በመቶ እና 45 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። የኢኮኖሚ ዕድገቱ በክፍላተ ኢኮኖሚ ሲታይ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በአማካይ በየዓመቱ የ5.9፣ የ13 እና የ10.6 በመቶ ዕድገት እንዲያስመዘግቡ ታቅዷል (ሠንጠረዥ 3)።

ሠንጠረዥ 3፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አማካይ ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች (በመቶኛ)

| | 2008-2012 | አማካይ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 |
| ግብርና | 1.5 | 1.7 | 1.6 | 1.6 |
| የሰብል ምርት | 1.1 | 0.9 | 0.7 | 0.8 |
| የእንስሳት ምርት | 0.2 | 0.7 | 0.9 | 0.8 |
| ኢንዱስትሪ | 3.4 | 3.2 | 4.8 | 4 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 0.8 | 1.5 | 2.9 | 2.2 |
| ኮንስትራክሽን | 2.6 | 1.7 | 1.7 | 1.7 |
| አገልግሎት | 3.3 | 4.3 | 4.6 | 4.4 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 1.3 | 1.7 | 2 | 1.9 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 0.6 | 0.9 | 1.1 | 1 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 0.4 | 0.3 | 0.2 | 0.3 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 8.2 | 9.2 | 10.9 | 10 |

ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

የ10 በመቶ አማካይ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማሳካት የሚያስፈልገው የኢንቨስትመንት ምጣኔ (gross capital formation) ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነጻጸር የሚኖረው ድርሻ በልማት ዕቅዱ ዘመን በአማካይ 36.9 በመቶ እንደሚሆን ተገምቷል። ይህም ባለፉት የልማት ዕቅዶች የትግበራ ወቅት ተመዝግቦ ከነበረው የኢንቨስትመንት ምጣኔ ጋር የሚስተካከል ሲሆን ባለፉት ዓመታት በተለይም በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች የታየውን የሀብት ብክነት የበዛበትና የተጓተተ አፈጻጸም የማረም አስፈላጊነትን ግምት ውስጥ በማስገባት የካፒታል ምርታማነትን በመጨመር እንደሚካካስ ታሳቢ ተደርጓል። ከጠቅላላው የኢንቨስትመንት ምጣኔ ውስጥ 64.8 በመቶ የሚሆነው ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ኢንቨስትመንት የሚጠበቅ ሲሆን ይህም በልማት ዕቅዱ የተቀመጠውን የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ልማት መሪነት የማረጋገጥ አቅጣጫ የተከተለ ነው። ቀሪው 35.2 በመቶ የመንግስት ኢንቨስትመንት ድርሻ ይሆናል። ከመንግስት ኢንቨስትመንት ድርሻ ውስጥ 63.1 በመቶ በመንግስት የካፒታል በጀት አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን ቀሪው 36.9 በመቶ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኢንቨስትመንት ድርሻ ነው።

ሠንጠረዥ 4፡ የመጨረሻ ጠቀሜታ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ጠቅላላ ፍጆታ | 79.1 | 72 | 70 | 71 | 69.3 |
| የግል ፍጆታ | 64.8 | 61.1 | 56.8 | 58.9 | 55.2 |
| የመንግሥት ፍጆታ | 9.5 | 10.9 | 13.2 | 12.1 | 14 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ | 20.9 | 28 | 30 | 29 | 30.7 |
| ጠቅላላ ኢንቨስትመንት | 30.8 | 36.8 | 37 | 36.9 | 37.3 |
| የግል ኢንቨስትመንት | 22.1 | 22.4 | 25.4 | 23.9 | 26.9 |
| የመንግስት ኢንቨስትመንት | 8.2 | 14.4 | 11.6 | 13 | 10.3 |
| በመንግስት ካፒታል በጀት | 4.2 | 7.7 | 8.6 | 8.2 | 8.4 |
| የመንግስት የልማት ድርጅቶች | 4 | 6.7 | 3 | 4.8 | 1.9 |
| ጠቅላላ የወጪ ንግድ | 7.1 | 11.9 | 12.9 | 12.4 | 12.9 |
| ጠቅላላ የገቢ ንግድ | 16.9 | 20.7 | 19.9 | 20.3 | 19.4 |
| ሀብት ክፍተት | (9.9) | (8.9) | (7) | (7.9) | (6.5) |


ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

በተጨማሪም የወጪ እና የገቢ ንግድ (አገልግሎትን ጨምሮ) ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ በ2022 በቅደም ተከተል 13 እና 19.4 በመቶ እንደሚሆን ታቅዷል። በዚህም የሀብት ክፍተት (ማለትም በሀገር ውስጥ ቁጠባና በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት መካከል ወይም በወጪ ንግዱ ገቢና በንግዱ ወጪ መካከል ያለው ልዩነት) ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በልማት ዕቅዱ ዘመን እየቀነሰ እንደሚመጣ ታቅዷል።

# 4.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 32.7 በመቶ ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 22 በመቶ እንደሚቀንስ ታቅዷል። በአንጻሩ በዚሁ ጊዜ የኢንዱስትሪ ድርሻ ከ29 በመቶ ወደ 35.9 በመቶ ሲያድግ በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ ከ39.5 በመቶ ወደ 42.1 በመቶ ከፍ እንደሚል ታቅዷል። ከኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በተናጠል ሲታይ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.9 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 17.2 በመቶ እንደሚያድግ ታቅዷል (ሠንጠረዥ 5 እና ሥዕል 4)።

ሥዕል 4፡ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

ሠንጠረዥ 5፡ የኢኮኖሚ ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | 2017 | 2022 |
|---|---|---|---|
| ግብርና | 32.7 | 27.2 | 22 |
| የሰብል ምርት | 21.3 | 16.6 | 12.4 |
| የእንስሳት ምርት | 8.5 | 8.5 | 8.2 |
| ኢንዱስትሪ | 29 | 30.4 | 35.9 |
| የማኑፋክቸሪንግ | 6.9 | 10.3 | 17.2 |
| የኮንስትራክሽን | 21.1 | 19.3 | 17.9 |
| አገልግሎት | 39.5 | 42.4 | 42.1 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 14.3 | 16.2 | 16.9 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 5.3 | 6.7 | 8 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 3.3 | 3.3 | 2.9 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት* | 100 | 100 | 100 |

ምንጭ፦ የፕላንና ልማት ኮሚሽን (*የተጣራ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት፣ FISIM ተቀንሶ)

በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ዘርፍ ለጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በአማካይ በየአመቱ የ1.6 መቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። በአንጻሩ የኢንዱስትሪና አግልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል የ4 መቶኛ ነጥብ እና የ4.4 መቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል (ሠንጠረዥ 6)።


ሠንጠረዥ 6፡ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የሚኖራቸው አስተዋጽዖ (በመቶኛ)

| | 2008-2012 | አማካይ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 |
| ግብርና | 4.1 | 5.5 | 6.2 | 5.9 |
| የሰብል ምርት | 4.8 | 4.6 | 4.6 | 4.6 |
| የእንስሳት ምርት | 2.5 | 8.5 | 10.1 | 9.3 |
| ኢንዱስትሪ | 15.2 | 11.4 | 14.6 | 13 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 13 | 18.4 | 22.9 | 20.6 |
| ኮንስትራክሽን | 17.3 | 8.5 | 9.2 | 8.9 |
| አገልግሎት | 8.2 | 10.4 | 10.7 | 10.6 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 8.9 | 11.3 | 11.8 | 11.6 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 11.5 | 14.6 | 14.8 | 14.7 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 12.5 | 9.9 | 7.8 | 8.8 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 8.2 | 9.2 | 10.9 | 10 |

ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

**የሸቀጦች የወጪ ንግድ በዋና ዋና ዘርፎች፡-** በልማት ዕቅዱ ዘመን ከታቀደው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር በተያያዘ የሸቀጦች የወጪ ንግድም መዋቅራዊ ወይም የስብጥር ለውጥ እንደሚኖረው ታቅዷል። በዚህ መሠረት  የሸቀጦች ወጪ ንግድ ከጠቅላላው ወጪ ንግድ ያለው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 39 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 53.9 በመቶ ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ከዚህም ውስጥ የግብርና፣ የማኑፋክቸሪንግ እና የማዕድን ዘርፎች የወጪ ንግድ ድርሻዎች በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከነበሩበት 77፣ 13.3 እና 6.9 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 36.4፣ 48.4 እና 11.3 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በአጠቃላይ የግብርና ምርቶች በወጪ ንግድ ገቢ ውስጥ ያላቸው ድርሻ እየቀነሰ እንደሚሄድና በአንጻሩ የኢንዱስትሪና የማዕድን ምርቶች ድርሻ እየጨመረ በመሄድ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ታቅዷል (ሥዕል 5)።


ሥዕል 5፡ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ስብጥር በዋና ዋና ዘርፎች (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

**የዘርፎች የሠራተኛ ስምሪት ድርሻ ለውጥ፦** ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር በተያያዘ የሰው ኃይል ስምሪት ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው ዘርፎች ከፍተኛ ምርታማነት ወደላቸው ዘርፎች እንደሚሸጋገር ይጠበቃል። በዚህ መሠረት በዕቅዱ ዘመን በግብርናው ዘርፍ የሚሰማራው የሰው ኃይል ድርሻ በ2005 በጀት ዓመት ከነበረበት 72.5 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 42.0 በመቶ ዝቅ እንደሚል ይጠበቃል። በአንጻሩ በዚህ ጊዜ በኢንዱስትሪ (ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን እና ማዕድን) የተሰማራው የሰው ኃይል ድርሻ ከ7.4 በመቶ ወደ 19.0 በመቶ ከፍ ሲል በአገልግሎት ዘርፍ የሚሰማራው የሰው ኃይል ድርሻ ደግሞ ከ20 በመቶ ወደ 39 በመቶ እንደሚጨምር ይጠበቃል።

ሥዕል 6፡ የዘርፎች የሠራተኛ ኃይል ስብጥር በ2022 (በመቶኛ)




ምንጭ፦ የፕላንና ልማት ኮሚሽን

## 4.3 የፊሲካል ፖሊሲ

በልማት ዕቅዱ ዘመን የመንግስትን ገቢና ወጪ ጤናማ እና ዘላቂ ለማድረግ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢን የሚያሳድግና በአንጻሩ የሀገራችን የዕዳ ጫናን ለመቀነስና በዘላቂነትም ጤናማ የብድር ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ አቅጣጫ ተቀምጧል። በዚህ መሠረት በታክስ ፖሊሲና ህጎች ዙሪያ ሪፎርም በማካሄድ፣ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን በማዘመን፣ የታክስ መዋቅሩን በማሻሻል እና ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴን በመከላከል ጠቅላላ የመንግስት ገቢን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 395 ቢሊዮን ብር በአማካይ በየዓመቱ በ26.1 በመቶ በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3.9 ትሪሊዮን ብር ለማድረስ ግብ ተቀምጧል። ይህን ግብ ለማሳካትም ከታክስ የሚገኘውን ገቢ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 312 ቢሊዮን ብር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3.5 ትሪሊዮን ብር ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን በዚሁ ጊዜም የታክስ ገቢ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ ከ9.2 በመቶ ወደ 18.2 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። ጠቅላላ የመንግስት ወጪን በተመለከተም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 480 ቢሊዮን ብር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 4.5 ትሪሊዮን ብር ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል።

በዚህ መሠረት ጠቅላላው የመንግስት ወጪ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት 23.4 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። በተመሳሳይ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የካፒታልና የመደበኛ ወጪዎች ከጠቅላላው የመንግስት ወጪ ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በቅደም ተከተል ወደ 36 በመቶ እና 64 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

### ሠንጠረዥ 7፡ ጠቅላላ የመንግስት ገቢና ወጪ ዕቅድ

| | 2012 | አማካይ (በቢሊዮን ብር) | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ጠቅላላ የመንግስት ገቢ | 395 | 764 | 2,547 | 1,655 | 3,934 |
| የሀገር ውስጥ ገቢ | 354 | 720 | 2452 | 1,586 | 3,818 |
| የታክስ ገቢ | 312 | 637 | 2223 | 1,430 | 3,492 |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | 43 | 83 | 229 | 156 | 326 |
| የውጭ ዕርዳታ ገቢ | 41 | 44 | 94 | 69 | 116 |
| ጠቅላላ ወጪ | 480 | 927 | 2,944 | 1,936 | 4,490 |
| የካፒታል ወጪ | 204 | 424 | 1,164 | 794 | 1,617 |
| የመደበኛ ወጪ | 276 | 504 | 1,781 | 1,142 | 2,874 |
| የበጀት ጉድለት | (85) | (164) | (398) | (281) | (556) |
| የወጪ አሸፋፈን | 85 | 164 | 398 | 281 | 556 |
| የሀገር ውስጥ የታክስ ገቢና የበጀት ጉድለት ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶ) | | | | | |
| የታክስ ገቢ | 9.2 | 11.6 | 16 | 13.8 | 18.2 |
| የበጀት ጉድለት | 2.5 | 3 | 2.9 | 2.99 | 2.9 |

ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር

የመንግስት በጀት ወጪ ድልድልም ድህነት ተኮርና ለዘላቂ ልማት መሠረት ለሆኑ ዘርፎች (ለሰው ሀብት ልማት፣ ለመሠረተ ልማት ማስፋፋት እና ለአምራች ዘርፎች ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ) እና አዳዲስ የዕድገት ምንጭ ለሆኑ ዘርፎች ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም የመንግስትን ወጪ ውጤታማነት ለማሳደግ በዕቅዱ የትግበራ ዓመታት የሪፎርም ሥራዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የመንግስት የበጀት ጉድለት ብር 556.4 ቢሊዮን ሆኖ እንደሚመዘገብ የተተነበየ ሲሆን ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻም 2.9 በመቶ ይሆናል። የበጀት ጉድለቱ አሸፋፈን በአብዛኛው ከሀገር ውስጥ ምንጮች እንደሚሆን አቅጣጫ ተቀምጧል። ለዚህም በገበያ ሥርዓት የሚመራ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቦንድና የአክሲዮን ገበያን ለመመስረት መንግስት በትኩረት ይሠራል። በዚህም መሠረት በልማት ዕቅዱ ዘመን በአማካይ 79 በመቶ የሚሆነው የበጀት ጉድለት ለዋጋ ግሽበት በማያጋልጡ የሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 21 በመቶ ከውጭ ሀገር በሚገኝ ብድር ይሸፈናል።

በሌላ በኩል በዕቅዱ መነሻ ወቅት ያለውን ከፍተኛ ሀገራዊ የዕዳ ክምችት ከማቃለል አኳያ የመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂን በመከተል ጤናማ የብድር ሁኔታ ለመፍጠር ይሠራል። በዚህም ጠቅላላው ሀገራዊ የዕዳ ክምችት ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 51 በመቶ ምጣኔ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 48.6 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

# 4.4 የገንዘብ ፖሊሲ እና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት

የገንዘብና የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎች እንዲሁም የፋይናንስ ኢንዱስትሪው ልማት የማክሮ ኢኮኖሚውን በማረጋጋት ሀገሪቱ በልማት ዕቅዱ ዘመን ላቀደችው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ብሎም ጤናማና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦች መሳካት የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የዋጋ ግሽበት በአማካይ ከነጠላ አኀዝ የዘለለ እንዳይሆን ለማድረግ የገንዘብ ፖሊሲው ይህን ግብ በሚያሳካ መልኩ ይቃኛል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት የበጀት ጉድለት የዋጋ ግሽበትን በማያስከትል መልኩ እንዲሸፈን ገበያ መር የመጀመሪያና የሁለተኛ የሰነዶች ሽያጭ ገበያ እንዲሳለጥ በማድረግ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የመንግስት የበጀት ጉድለት በዋናነት ከገበያ እንዲሸፈን ይሠራል፡፡

የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመንን ለማረጋገጥ እና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ በገበያ ፍላጎትና አቅርቦት የሚመራ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የፋይናንስ ኢንዱስትሪው የታቀደውን መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያግዝ ለማድረግ የወለድ ምጣኔ ተመን በገበያ ፍላጎትና አቅርቦት እንዲመራ ይደረጋል፤ የዲጂታል ፋይናንስ ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡ ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበ የካፒታል አካውንት ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግና የተሳለጠ የካፒታል ገበያ በመፍጠር አማራጭ የልማት ፋይናንስ ምንጮችን ለማስፋት ይሠራል፡፡

የተረጋጋና በነጠላ አኀዝ የተገደበ የዋጋ ሁኔታ ከማረጋገጥ አንጻር በዕቅዱ ዘመን አጠቃላይ የገንዘብ አቅርቦት መጠን (broad money) በአማካይ በየዓመቱ በ21 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ በዕቅዱ ዘመን የመሠረታዊ ገንዘብ (base money) የመስፋፋት ምጣኔ በአማካይ በየዓመቱ በ19 በመቶ እንዲያድግ እና መሠረታዊ ገንዘብ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት በነበረበት 7.3 በመቶ ለማቆየት ግብ ተጥሏል (ሠንጠረዥ 8)፡፡ ይህም ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲን በመከተል የዋጋ ግሽበትን በነጠላ አኀዝ ለመገደብ ከተያዘው አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 8፡ የገንዘብ አቅርቦት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ (በመቶኛ)

| ዝርዝር | 2012 | 2013 -2017 | 2018 -2022 | 2013-2022 |
|---|---|---|---|---|
| መሠረታዊ የገንዘብ አቅርቦት (base money) | 7.3 | 7.3 | 7.3 | 7.3 |
| ጠቅላላ የገንዘብ አቅርቦት (broad money) | 30.8 | 34.3 | 36.8 | 35.5 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በገበያ ዋጋ | 100.0 | 100.0 | 100.0 | 100.0 |

ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

የፋይናንስ ኢንዱስትሪው ከበጀት ውጪ ለሚከናወኑ በግሉ ዘርፍና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ለሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትልቅ የፋይናንስ አቅምን ከማረጋገጥ አንጻር በልማት ዕቅዱ ዘመን የባንኮችን ዓመታዊ ቁጠባ በአማካይ በ28.6 በመቶ እና የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትን ዓመታዊ ቁጠባ በአማካይ በ30 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ መጠን (Deposit position) በ2012 ከነበረበት ብር 1.04 ትሪሊዮን በአማካይ በየዓመቱ በ22.4 በመቶ በማሳደግ በ2022 ወደ ብር 7.9 ትሪሊዮን ለማድረስ ታቅዷል፡፡

## 4.5 የልማት ፋይናንስ

በዕቅዱ በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በመሠረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአካባቢ ጥበቃና ልማት፣ በዘላቂ ሰላም፣ በመልካም አስተዳደር፣ በፍትሕና ቀጠናዊ ትስስር ግንባታ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ ፋይናንስ ነው። የፋይናንስ ዕቅድ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህም በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድና ከበጀት ውጭ የሆነ የፋይናንስ ዕቅድ ናቸው።

**በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድ፡-** በመንግሥት ገቢና ወጪ ትንበያ መሠረት በልማት ዕቅዱ ዘመን ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ የውጭ እርዳታን ጨምሮ የጠቅላላ ወጪን 88.7 በመቶ እንደሚሸፍንና ቀሪው 11.2 በመቶ በበጀት ጉድለት እንደሚታይ ትንበያው ያሳያል። ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ በዕቅድ ዘመኑ ብር 19.3 ትሪሊዮን የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ውስጥ መደበኛ ወጪ ብር 11.4 ትሪሊዮን እና የካፒታል ወጪ ብር 7.9 ትሪሊዮን እንደሚሆን የመንግሥት ገቢና ወጪ ትንበያ ያመለክታል።

በዕቅዱ ዘመን በየዘርፉ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያ በዘርፍ ተነጥሎ ሲታይ ለዕቅዱ ዘመን ከተተነበየው ብር 7.9 ትሪሊዮን ከጠቅላላው የመንግስት የካፒታል ወጪ ውስጥ የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች የ24.8 በመቶ እና የመሠረተ ልማት ዘርፎች የ43.3 በመቶ ድርሻ እንደሚኖራቸው ትንበያው ያሳያል። የሰው ሀብት ልማት ዘርፍ ከጠቅላላው የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያ ውስጥ 21.9 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይወስዳል። ሌሎች በዕቅዱ ውስጥ የተካተቱ የልማት ሥራዎች ቀሪውን 10 በመቶ የካፒታል ወጪ ድርሻ እንደሚይዙ የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያው ያሳያል። ዝርዝሩ ቀጥሎ (በሠንጠረዥ 9) ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 9፥ የበጀት ነክ የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያ በዘርፍ ከጠቅላላ የካፒታል ወጪ ያለው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ኢኮኖሚ ልማት | 12.9 | 24.5 | 25 | 24.8 | 23.6 |
| መሠረተ ልማት | 52.8 | 41.6 | 45 | 43.3 | 49.7 |
| ሰው ሀብት ልማት | 23.1 | 23.8 | 20 | 21.9 | 16.7 |
| ሌሎች ዘርፎች | 11.2 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| ጠቅላላ የካፒታል ወጪ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር

**ከበጀት ውጪ የሆነ የፋይናንስ ምንጭና የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ፍላጎት፡-** በአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን ከበጀት ውጭ የሆነ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ፋይናንስ ከባንክና ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቁጠባና ከሌሎች ቁጠባ ምንጮች በጠቅላላ 18 ትሪሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል። ከዚህ ውስጥ ባንኮችና አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት በቁጠባና ብድር ተመላሽ የሚሰበስቡት ብር 15.6 ትሪሊዮን (86.5 በመቶ) ድርሻ አለው። ቀሪው ብር 2.4 ትሪሊዮን ብር (13.5 በመቶ) ከግምጃ ቤት ሰነድ፣ ከመንግስት ቦንድ ሽያጭ፣ ከካፒታል ገበያ (equity market) እና ከሌሎች የፋይናንስ ምንጮች እንደሚሰበሰብ ትንበያው ያሳያል።

ሠንጠረዥ 10፡ በጀት ነክ ያልሆነ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ (በቢሊዮን ብር)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ተቀማጭ ሒሳቦች | 144.6 | 334.8 | 1061.7 | 699 | 1588 |
| ባንኮች | 141.8 | 328.2 | 1037.1 | 683 | 1549.2 |
| አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | 2.8 | 6.6 | 24.6 | 16 | 38.8 |
| ከብድር የተሠበሠበ | 200.7 | 417.1 | 1299.6 | 858 | 1947 |
| ባንኮች | 183.3 | 376.2 | 1147.9 | 762 | 1707.4 |
| አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | 17.4 | 40.9 | 151.7 | 96 | 239.6 |
| ሌሎች የፋይናንስ ምንጮች | 59 | 128.8 | 357.8 | 243 | 526.6 |
| አጠቃላይ የፋይናንስ ምንጭ | 404.3 | 880.7 | 2719.1 | 1800 | 4061.6 |

ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ከበጀት ውጭ የሚቀርበው ጠቅላላ የብድር ፋይናንስ በልማት ዕቅዱ ዘመን 14 ትሪሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለግብርና ዘርፍ 3.4 ትሪሊዮን ብር ብድር ለማቅረብ ዕቅድ ተይዟል። ይህም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት 24.3 በመቶ ይሆናል። ለኢንዱስትሪ 5.7 ትሪሊዮን ብር (40.7 በመቶ) እና ቀሪው 4.9 ትሪሊዮን ብር (35 በመቶ) ለአገልግሎት ዘርፍ እንደሚውል ዕቅድ ተይዟል። በሠንጠረዥ 11 እንደተመለከተው የፋይናንስ ድልድሉ በተቋማዊ ባለቤት ሲታይ 12.2 ትሪሊዮን ብር (87.2 በመቶ) የግሉን ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ለማሟላት የሚውል ሲሆን 1.8 ትሪሊዮን ብር (12.8 በመቶ) በመንግስት የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወጪ ለመሸፈን እንደሚውል በዕቅድ ተይዟል። በአጠቃላይ በአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ዘመን የታቀደውን የኢንቨስትመንት ምጣኔ ከሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት፣ ከካፒታል በጀት፣ ከውጭ ቀጠባ እና ከራስ ጥሪትና ከሌሎች የኢንቨስትመንት ምንጮች በሚገኝ የልማት ፋይናንስ የሚሸፈን ይሆናል።

ሠንጠረዥ 11፡ የሀገር ውስጥ ብድር ድልድል (በቢሊዮን ብር)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ጠቅላላ ብድር አቅርቦት | 290.8 | 591.0 | 2214.2 | 1402.6 | 3262.1 |
| ለግብርና | 34.2 | 122.0 | 553.68 | 337.9 | 880.8 |
| ለኢንዱስትሪ | 155.1 | 289.3 | 857.9 | 573.6 | 1295.1 |
| ለማኑፋክቸሪንግ | 27.2 | 137.3 | 683.36 | 410.3 | 1131.2 |
| ለአገልግሎት | 101.5 | 179.7 | 802.6 | 491.1 | 1086.2 |
| የብድር አቅርቦት (በተቋማዊ ባለቤትነት በቢሊዮን ብር) | | | | | |
| ጠቅላላ ብድር | 290.8 | 591 | 2214.2 | 1402.6 | 3262.1 |
| ለመንግስት ዘርፍ | 96.1 | 115.22 | 242.92 | 179.07 | 326.2 |
| ለየግሉ ዘርፍ | 194.7 | 475.76 | 1971.3 | 1223.53 | 2935.9 |

ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

## ሠንጠረዥ 12፡ የኢንቨስትመንት ምንጮች

| | እማካይ (በቢሊዮን ብር) | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|
| | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ኢንቨስትመንት | 1,994 | 5,017 | 3,506 | 7,149 |
| ከሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት | 591 | 2,214 | 1,403 | 3,262 |
| ከካፒታል በጀት | 424 | 1,163 | 794 | 1,617 |
| የውጭ ሀብት ቁጠባ | 467 | 944 | 705 | 1,250 |
| ከራስ ጥሪትና ከሌሎች የኢንቨስትመንት ምንጮች | 512 | 696 | 604 | 1,020 |
| የኢንቨስትመንት (ፋይናንስ) ምንጮች ድርሻ (በመቶኛ) | | | | |
| ኢንቨስትመንት | 36.8 | 37 | 36.9 | 37.3 |
| ከሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት | 10.6 | 16.1 | 13.4 | 17 |
| ከካፒታል በጀት | 7.7 | 8.6 | 8.2 | 8.4 |
| የውጭ ሀብት ቁጠባ | 8.9 | 7 | 8 | 6.5 |
| ከራስ ጥሪትና ከሌሎች | 9.7 | 5.3 | 7.5 | 5.3 |

ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

# ምዕራፍ አምስት

## የአስር ዓመቱ የኢኮኖሚ
## ዘርፍ ልማት ዕቅድ

# 5.1 የግብርና ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የግብርና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የመስኖ አቅምን በማጎልበት ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፤ የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፤ በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ አርሶ አደሮች የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው በማገዝ ወደ ኢንቨስተርነት ማሳደግ፤ የእንስሳት ሃብት ልማትን፣ የመኖ ልማትንና ጤናን ማሻሻል፤ የሆርቲካልቸር ልማትን ማስፋፋት፤ በግብርና ልማት ባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፤ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን መገንባት፤ የሥራ ዕድል መፍጠር እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ልማት ማካሄድ ናቸው።

የግብርና ልማት ዋና ዋና ዓላማዎች ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፤ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ፤ በተለይም ግብርናን በማዘመን ሀገራዊ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ፍላጎትን ማሟላት፤ ለኢንዱስትሪ ግብዓት ማቅረብና እሴትን በመጨመር ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ማቅረብ፤ በገጠር በቂ የሥራ ዕድል መፍጠርና የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን በመቀነስ ግብርናውን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ማድረግ ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የግብርና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

○ በሁሉም የአመራረት ሥርዓቶች እና የሰብል ዓይነቶች የሰብል ምርትን ከ543 ሚሊዮን ወደ 925 ሚሊዮን ኩንታል ማሳደግ፤

- የአዝርዕት ምርትን ከ362 ሚሊዮን ወደ 662 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- ከአዝርዕት ምርት ውስጥ በመኸር ወቅት የሚመረተውን ከ333 ሚሊዮን ወደ 586 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- በበልግ የሚመረተውን ምርት ከ21 ሚሊዮን ወደ 37 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- በመስኖ የሚመረተውን ምርት ከ8 ሚሊዮን ወደ 38 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- ከአጠቃላይ የሰብል ምርት ውስጥ የመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻ ምርት ድርሻን ከ4 በመቶ ወደ 16 በመቶ ማሳደግ፣
- የምርጥ ዘር አቅርቦት ከ1.09 ሚሊዮን ወደ 2.3 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- የአፈር ማዳበሪያ ሥርጭት ከ16.1 ሚሊዮን ወደ 32.9 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- እንደ ኮምፖስት ያሉ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና የመሬት አጠቃቀምን በማሻሻል የኬሚካል ማዳበሪያ ፍላጐትን ለመቀነስ መጠነ ሰፊ ጥረት ማድረግ፣
- የተዛማች ተባዮች ፀረ-ተባይ መጠን ከ15.4 ሺህ ወደ 100 ሺህ ሊትር እንዲሁም የመደበኛ ተባዮች ፀረ-ተባይ መጠን ከ4.9 ሚሊዮን ወደ 5.5 ሚሊዮን ሊትር ማሳደግ፣

○ የሆርቲካልቸር ምርትን ከ181 ሚሊዮን ወደ 261 ሚሊዮን ኩንታል ማሳደግ፤

- ለሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ልማት ለባለሃብት የተላለፈ መሬት ከ17.6 ሺህ ወደ 43 ሺህ ሄክታር ማሳደግ፣
- ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የሆርቲካልቸር ምርት ከ272.8 ሺህ ወደ 1.05 ሚሊዮን ቶን ማድረስ፣

- ከሆርቲካልቸር የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከ326.1 ሚሊዮን ወደ 950 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማድረስ፣
- የአነስተኛ ይዞታ የሆርቲካልቸር ምርት በመኸር ከ68 ሚሊዮን ወደ 112 ሚሊዮን ኩንታል እና በበልግ የሚመረተውን ምርት ከ47 ሚሊዮን ወደ 54 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣
- በመስኖ የለማ ሆርቲካልቸር ከ65 ሚሊዮን ወደ 95 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣

○ የእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ምርት መጠንና አይነት እንዲሁም ምርታማነትን ማሳደግ፤

- በእያንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር እጅ የሚገኙ የታላቢ ላሞችን አጠቃላይ ቁጥር ከ11.5 ሚሊዮን ወደ 9 ሚሊዮን ዝቅ በማድረግ፣ ከዚህም ውስጥ ዝርያቸው የተሻሻሉ እንስሳት ድርሻ ከ2.7 በመቶ ወደ 17 በመቶ ማሳደግ፣
- ከላም፣ ፍየልና ግመል የሚገኘውን አጠቃላይ ዓመታዊ የወተት ምርት ከ4.37 ቢሊዮን ሊትር ወደ 11.8 ቢሊዮን ሊትር ማድረስ፣
- በአማካይ በቀን ከአንድ ላም የሚገኝ የወተት ምርትን ከሀገር በቀል ላሞች ከ1.45 ሊትር ወደ 2.02 ሊትር፣ ከተዳቀሉ ላሞች ከ6 ሊትር ወደ 10.7 ሊትር እና ሙሉ በሙሉ የውጭ ዝርያ ከሆኑ ላሞች ከ13 ሊትር ወደ 17 ሊትር ማድረስ፣
- ከዳልጋ ከብት፣ ፍየል፣ በግ እና ግመል የሚገኘውን የስጋ ምርት ከ295 ሺህ ወደ 1.7 ሚሊዮን ቶን ማሳደግ፣
- የእንቁላል ምርት ከ2.8 ቢሊዮን ወደ 5.5 ቢሊዮን እንዲሁም የዶሮ ሥጋ ምርትን ከ48 ሺህ ወደ 106  ሺህ ቶን ማሳደግ፣
- ከመደበኛ የውሃ አካላት የሚገኘውን የዓሳ ምርት መጠን ከ59 ሺህ ወደ 247 ሺህ ቶን ማድረስና እንዲሁም ከአኳካልቸር የሚገኘውን ዓሳ ምርት 13 ሺህ ቶን ማድረስ፣
- የማር ምርትን ከ59 ሺህ ወደ 152 ሺህ ቶን ማድረስ፤

○ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ አርሶ እና አርብቶ አደሩን የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጅዎችንና የተሻሻሉ አሠራሮችን ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ዓመታዊ የአፈር ብክለትን በሄክታር ከነበረበት 20.5 ቶን CO2E ወደ 15.84 ቶን CO2E ዝቅ ማድረግ፣

○ ዓመታዊ ተጨማሪ የባዮማስ መጠንን ከ27 ሚሊዮን ወደ 75.2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ካርበን ከፍ በማድረግ በየዓመቱ ተጨማሪ የአፈር ካርቦናዊ ቁስ ይዘትን ከ1.8 በመቶ ወደ 2.18 በመቶ ማሳደግ፣

○ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን ለማሻሻል ለ10 ሺህ ተፋሰሶች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራትን ማቋቋም፣

○ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥራዎችን በመደበኛ ሥራዎች ዕቅድ ውስጥ በማካተትና በመተግበር የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ አቅምን ከ36.84 ሚሊዮን ወደ 125.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማሳደግ፤

- በሰብል ልማት ዘርፍ የሙቀት ጋዝ ቅነሳ ከ7.23 ሚሊዮን ወደ 37.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማድረስ፣
- በእንስሳት ልማት ዘርፍ የሙቀት ጋዝ ቅነሳ ከ12.06 ሚሊዮን ወደ 48 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማድረስ፣
- በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ዓመታዊ ተጨማሪ የተገለለ የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ከ17.55 ሚሊዮን CO2E ወደ 40 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን CO2E ማሳደግ፤

# 5.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች በየደረጃው የመፈጸም እና የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ፤ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፤ የነባር ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤ የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያና የመድሃኒት ምርቶችን ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ በማምረት የሀገር ውስጥ ፍላጎቶችን ማሟላትና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤ የሀገር ውስጥ ግብዓቶችን ለሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አምራቾች ቅድሚያ ትኩረት መስጠት፤ የወጪ ንግድ ምርቶችን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት ማሳደግ እና የማኑፋክቸሪንግ የእሴት ሰንሰለት፣ ትስስርና ተመጋጋቢነትን ማጠናከር፤ በጥናት ላይ የተመሠረቱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና የአሰራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በማኑፋክቸሪንግ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በብዛት፣ በጥራትና በአይነት መሳብ፤ ለዚህም የግሉን ዘርፍ ሚናና አጋርነት ማሳደግ፤ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ውስጣዊ ትስስር ለማሳለጥ በቀጣይ ከባድ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ፣ የኬሚካልና የፋርማሲቲካልስ እንዲሁም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ልማት ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር፤ የክላስተር አደረጃጀትን ማጠናከር፤ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት እና በሂደት ወደ ቀጣዩ ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ምቹ መደላድል መፍጠርና የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ ናቸው።

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎች የነባር አምራቾችን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል ጥራት ያላቸው አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ለሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ማስቻል፤ ስትራቴጂያዊ የሆኑ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤ የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ማምረት እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ በስፋት እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚያደርገውን አስተዋጽዖ ማሳደግ እና የኢንዱስትሪው ልማት ከዘላቂና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ናቸው። የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን አማካይ የማምረት አቅም አጠቃቀም ከ50 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣
- ስትራቴጂክ የሆኑ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የሀገር ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶችን ጠቅላላ የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ከ30 በመቶ ወደ 60 በመቶ ማሳደግ፣
- የምርት ጥራትን በማሻሻል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስተሪውን ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣
- ጥራት ያለው ኢንቨስትመንት በመሳብና ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውጤት በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ በማተኮር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት ከ2 ሺህ ወደ 11 ሺህ ማሳደግ፣
- በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በየዓመቱ የሚፈጠረውን አዳዲስ የሥራ ዕድል ከ172 ሺህ ወደ 850 ሺህ በማሳደግ በአጠቃላይ በዕቅዱ ዘመን በኢንዱስትሪው በድምሩ 5 ሚሊዮን አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር።

# 5.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የተሳለጠ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤ ሥነ-ምግባር የተላበሰ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት፤ በሀገር አቀፍና በክፍል አህጉር ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት እና ሰፊ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ምርታማ የሆነ ፍትሐዊ ገቢ የሚፈጥር፣ ምቹና አዳጊ የሥራ ዕድል መፍጠር ናቸው።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎች የኢንዱስትሪውን ሀገራዊ አቅም በመገንባት በሀገር በቀል ኩባንያዎች አብዛኛው የሀገር ውስጥ ፍላጎት እንዲሸፈን እንዲሁም በክፍል-አህጉሩ የተሻለ ድርሻ እንዲኖራቸው በማስቻል እና ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ግብዓቶች ውስጥ አብዛኞቹ በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ በማድረግ ኢንዱስትሪው ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፋጠን ተገቢውን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ማስቻል ናችው። በተጨማሪም ኢንዱስትሪው ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ በጥናትና ምርምር በመታገዝ እና የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገሮችን ልምድ በመቅሰም የኮንስትራክሽን ግንባታዎችን የጥራት፣ የወጪ እና የጊዜ ተወዳዳሪነት ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሻሻል ከአላማወቹ አንዱ ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የህብረተሰቡንና የአካባቢን ደህንነትና ጤንነት ያረጋገጠ የሥራ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና በጎ ገጽታ ለመገንባት እንዲችል የኢንዱስትሪው ተዋናዮችን እርካታ ወደ 75 በመቶ ማሳደግ፣
- በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከሚከሰቱ ግጭቶች ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት ሳይደርሱ በስምምነት መፍትሄ የሚሰጣቸውን 75 በመቶ ማድረስ፣
- በጥንቃቄና በጥራት ጉድለት በሰውና በንብረት ላይ የሚፈጠር አደጋን በ80 በመቶ መቀነስ፣
- በዓለምአቀፍ መመዘኛ እንደ ሀገር የተሳለጠ አማካይ የአሰራር ሥርዓት አፈጻጸም ከ49 በመቶ ወደ 75 በመቶ ከፍ ማድረግ፣
- በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን ብልሹ አሰራር ለመቀነስ እንደ ሀገር የተመዘገበውን የሙስና የአረዳድ ምዘና (corruption perception index) ውጤት ከ114ኛ ደረጃ (37 ነጥብ) ወደ 35ኛ ደረጃ (60 ነጥብ) ከፍ ማድረግ፣
- የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በሀገር ውስጥና በክፍል-አህጉር ደረጃ ያላቸውን የተወዳዳሪነት አቅም በማሳደግ የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻቸው ወደ 75 በመቶ እና በክፍል-አህጉር ደረጃ ወደ 25 በመቶ ከፍ ማድረግ፣
- የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የጊዜ ብክነት ወደ 50 በመቶ እንዲቀንስ ማድረግ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሥራ ዕድል ፈጠራ በየዓመቱ 16.6 በመቶ እንዲያድግ በማድረግ በኢንዱስትሪው በየዓመቱ በቀጥታ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ከ710 ሺህ ወደ 3.3 ሚሊዮን እንዲሁም በተዘዋዋሪ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ከ1.78 ሚሊዮን ወደ 8.3 ሚሊዮን ማድረስ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን 80 በመቶ የሚሆነውን መሠረታዊ የግንባታ ግብዓት ፍላጎት በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን።

# 5.4 የማዕድንና ነዳጅ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የማዕድንና ነዳጅ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የውጭ ምንዛሪ ግኝትና የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ፣ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ፣ ዕሴት የሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ እና የሥራ ዕድል መፍጠር ናቸው። የማዕድንና ነዳጅ ልማት ዓላማዎች የማዕድንና ነዳጅ ሀብቶችን ለይቶ በማወቅ፣ በማልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጡን ማፋጠንና ሀገራዊ ሃብትን ማሳደግ እንዲሁም ለውጭ ምንዛሪ ግኝትና ለሀገር ውስጥ ገቢ የሚኖረውን አስተዋጽዖ በማጉላት፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በማሳደግ፣ አስፈላጊ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የማዕድንና ነዳጅ ልማት ምርቶች እሴት እንዲጨምሩ በማድረግ እና የሥራ ዕድል በመፍጠር የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፋይዳውን ማሳደግ ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የማዕድንና ነዳጅ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስተሮች ብዛት ከ160 ወደ 660 እንዲሁም የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮችን ብዛት ከ50 ወደ 1,050 ማሳደግ፣
- በማዕድንና ነዳጅ ልማት በአገልግሎት መስክ የሚሰማሩ ኢንቨስተሮችን ብዛት ከ1,700 ወደ 6,700 ማሳደግ፣
- በኩባንያዎችና ባህላዊ አምራቾች የሚመረተውን የወርቅ ምርት መጠን ከ3.2 ቶን ወደ 137 ቶን ማድረስ፣
- የማዕድናትን ክምችት ሃብት የሥነ-ምድር መረጃ ማደራጀት ከነበረበት 10 በመቶ ወደ 40 በመቶ ማሳደግ፣
- ለኮንስትራክሽን፣ ለኬሚካል፣ ለፔትሮኬሚካል፣ ለኃይል ማመንጫ እና ለሌሎች ተዛማጅ ምርቶች ግብዓት የሚሆን የአለኝታ ክምችት ቦታዎች የመለየት ጥናቶችን ከ600 ወደ 6,000 ከፍ ማድረግ፣
- የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን እሴት የሚጨምሩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ቁጥር ከ30 ወደ 130፤ የኮንስትራክሽን ግብዓት የሚያመርቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት ከ1,500 ወደ 6,500 እንዲሁም ለኬሚካልና ለፔትሮኬሚካል ምርት የሚረዱ ማዕድናትን የሚያመርቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት ከ100 ወደ 1,100 ማሳደግ፣
- የኃይል ምንጭ ማዕድናትን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች እስካሁን ያልነበሩ ሲሆን በ2022 በጀት ዓመት የእነዚህን ኢንዱስትሪዎች ብዛት 10 ማድረስ እና የጨው ምርትን ጥራትና መጠን በመጨመር ከውጭ የሚገባውን የጨው ምርት ሙሉ በሙሉ ማስቀረት፣
- የማዕድንና ነዳጅ ልማት የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል ከነበረበት 200 ሺህ ወደ 1.8 ሚሊዮን ማሳደግ።

# 5.5 የንግድ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የንግድ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የመፈጸምና የማስፈጸም ተቋማዊ አቅምን ማሳደግ፤ ዕድገቱን ማሳለጥ የሚያስችሉ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፤ የንግድ አሠራሮችን ማዘመን፤ የወጪ ንግድ የምርት መጠን፣ ስብጥርና ጥራትን ማሳደግ፤ ጤናማ ውድድር የሰፈነበት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት አመቺ የሆነ የንግድ ሥርዓት መዘርጋት እና የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማረጋገጥ ናቸው። በተጨማሪም ዘመናዊ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት የምርትና አገልግሎት ጥራትና ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ በማጠናከር፤ የኢንስፔክሽንና የሬጉሌሽን ሥራን በማሻሻል፤ የተንዛዛውን የግብይት ሰንሰለት ሪፎርም በማድረግ እና የንግድ ተወዳዳሪነትን በማስፈን የሸማቹን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይሠራል። በሌላ በኩል የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን፤ ከአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና ሙሉ ተጠቃሚ መሆን እና ከተመረጡ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት በማድረግ ለሀገራችን ምርቶች ሰፊ የገበያ ዕድል መፍጠር ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል።

የንግድ ልማት ዓላማዎች በሀገር ውስጥ ዘመናዊ፣ ፍትሐና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ አሠራርና የግብይት ሥርዓትን በማስፈን፤ በዕሴት ጭማሪ የላቁ የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ለዓለም ገበያ ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ፤ የዓለም አቀፍና ከባቢያዊ ትስስርን የሚያጎለብቱ የንግድ ስምምነቶችን በማጠናከር የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የንግድ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የንግድ ሥራን ለመጀመር ያለ አመቺነት ነጥብን ከ48 ወደ 80 በማሻሻል ኢትዮጵያን በ2022 በጀት ዓመት ከ50 ሀገሮች ተርታ ማሰለፍ፣
- በሀገር ውስጥ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን የምርት ጥራታቸውን፣ ደህንነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ በቁጥር ከ300 ወደ 610 ማሳደግ፣
- በሀገር ውስጥ ለተመረቱ እና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶች የሚደረግ የኢንስፔክሽን ሥራን ከ28 የምርት ዓይነቶች ወደ 68 የምርት ዓይነቶች በማሳደግ በገቢ ምርቶች ላይ የሚደረግ የምርት ጥራት ፍተሻን ከ2 ሚሊዮን ወደ 3.5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ከፍ ማደረግ፣
- የወጪ ምርቶች ላይ የሚደረግ የምርት ጥራት ፍተሻን ከ650 ሺህ ወደ 1.1 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማሳደግ፣
- የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ተግባርን በቁጥር ከ1.1 ሚሊዮን ወደ 2.1 ሚሊዮን ማሳደግ፣
- ፀረ-ውድድር የንግድ ተግባራትን እና የሸማች መብት ጥሰቶችን በመከላከል የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ የገበያ ግልጽነት ሽፋንን ከ40 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣

- የሀገር ውስጥና ድንበር ተሻጋሪ የቅድመ እና የድህረ ውህደት ቁጥጥር አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ከ96 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣
- በአጠቃላይ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢን ከ3 ቢሊዮን ወደ 18.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በማሳደግ በ2022 ከግብርና 6.7 ቢሊዮን፣ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ 9.0 ቢሊዮን፣ ከማዕድን 2.1 ቢሊዮን እና ከኤሌክትሪሲቲና ከሌሎች ሸቀጦች 0.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት፣
- ለሀገራችን ምርቶች የገበያ ዕድል ለማስፋት የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድሮችን በማጠናቀቅ፣ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቶችን ተግባራዊ በማድረግ፣ ከተመረጡ 7 ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነቶችን በመፈራረም እና ገበያ የማስተዋወቅ ሥራዎችን በማከናወን ዋና ዋና የውጭ ገበያ መዳረሻዎችን ብዛት ከ37 ወደ 96 ማሳደግ፣
- የዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ደረጃዎችንና ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ በፍላጐት ላይ የተመሰረቱ 3,055 ሀገራዊ አዳዲስ ደረጃዎችን ማዘጋጀት።

## 5.6 የቱሪዝም ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የቱሪዝም ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የባህል ሀብቶችን በማጥናትና በመንከባከብ ለሀገር ልማት አስተዋፅኦ ያላቸው ማህበራዊ ሀብቶችን በአግባቡ ለመለየትና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውን ለማጎልበት የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኝታዎች በአግባቡ መለየትና ማልማት፤ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት ማጠናከርና ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት በሀገሪቱ የሚገኙ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን በማልማት እና ነባር መዳረሻዎችን በማጎልበት ብሎም የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነትና መጠን በማስፋፋት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፤ ውጤታማ የገበያ ትስስር፣ ብራንዲንግና ፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን መፍጠርና የገበያ ድርሻን ማሳደግ እና ቱሪዝምን በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር በመደገፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ማሳደግ ናቸው።

በተጨማሪም በቱሪዝም የተሠማራውን የሰው ኃይል በዕውቀት እና በክህሎት በማብቃት የአገልግሎት አሠጣጡን ማሳለጥ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ ወጥ በሆነ አደረጃጀት ማዋቀር፣ የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ ማዘመን፣ የመንግስትን ድርሻ መቀነስ እና የመንግስትን እና የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር ትኩረት ይሰጣቸዋል። የቱሪዝም ልማት ዓላማዎች የሀገራችንን የቱሪዝም ሃብቶች በባለድርሻ አካላትና በማህበረሰቡ ተሳትፎ በማልማት፣ ተወዳዳሪ የሰው ኃይል በመፍጠርና የቱሪስት አገልግሎቶችን ጥራት በማጎልበት እንዲሁም ጠንካራ የገበያና የፕሮሞሽን ስትራቴጂዎችን በመተግበር፣ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን በማሳደግና ከቱሪዝም የሚገኙትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ማሳደግ ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የቱሪዝም ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የቋንቋዎችን ልማትና አጠቃቀም የሚያሻሽሉ ተግባራት የሚከናወንባቸውን ቋንቋዎች ብዛት ከ53 ወደ 73 ማድረስ፣

- የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብዛት ከ1,348 ወደ 2,696 ማሳደግ እና የጎብኝዎችን እርካታ መጠን ከ50 በመቶ ወደ 75 በመቶ ከፍ እንዲል ማድረግ፣
- 59 አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማልማትና በ40 ነባር መዳረሻዎች ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ተደራሽ ማድረግ፣
- የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን በማስተዋወቅና የጉብኝት ባህል እንዲዳብር በማድረግ የጎብኚዎችን ቁጥር ከ24 ሚሊዮን ወደ 70 ሚሊዮን ማሳደግ፣
- በሆቴል እና ቱሪዝም ሙያ ሠልጥነው አገልግሎት የሚሰጡ ሙያተኞችን ከ23 በመቶ ወደ 59 በመቶ ማሳደግ፣
- በቱሪዝም ልማት የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ከ1.6 ሚሊዮን ወደ 5.2 ሚሊዮን ማሳደግ፣
- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ጎብኚዎችን ቁጥር ከ850 ሺህ ወደ 7.3 ሚሊዮን እንዲጨምር ማድረግ፣

## 5.7 የከተማ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የከተማ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የከተሞችን ልማት እንቅስቃሴ በሚያፋጥን መልኩ ሚዛኑን የጠበቀና ያልተማከለ የአከታተም ሥርዓትን የሚያጠናክር ዕቅድና ትግበራ በሁሉም ደረጃ እንዲኖር በማድረግ በከተሞች የሚስተዋለውን የቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ለማጥበብ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የተለያዩ የቤት ፕሮግራሞች እና የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮች እንዲኖሩና የገበያ ትስስርን በማጠናከር የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕድገትን ማፋጠን፤ በተያያዘም የገጠር ማዕከላት መኖሪያ ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማትና አገልግሎትን በበቂ ሁኔታ ማቅረብ፤ የከተማ መሠረተ ልማቶች የግንባታ እና የጥገና ደረጃ ወጥቶላቸው በበቂ ሁኔታ እንዲቀርቡ እና በዕቅድ፣ በዲዛይን እና በድርጊት መርሐ-ግብር እንዲቀናጁ ማድረግ በከተማ መሠረተ ልማት አቅርቦት የግሉን ዘርፍ ሚና በማጎልበት እና የከተማ መሠረተ ልማት አማራጭ ፋይናንስን በማስፋት አረንጓዴ ልማትን የሚያፋጥን የልማት ስትራቴጂ እንዲሁም ከተሞች ያልተማከለና መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍን ዘመናዊ አደረጃጀት ብሎም የአመራርና የባለሙያ ስምሪት እንዲኖራቸው ማስቻል፤ የካፒታልና የሰው ኃይል ፍልሰትን በየአካባቢው በመግታት የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ማስፋፋት፤ አነስተኛና መካከለኛ ከተሞችን ማልማት እና የከተሞችን ልማት ለማፋጠንና ፍትሐዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመሬት አቅርቦት በበቂ መጠንና በዘላቂነት ማቅረብ ናቸው።

የከተማ ልማት ዓላማዎች የከተሞች ልማት እና የገጠር ዕድገትን የሚያፋጥን እንቅስቃሴ በከተማ እና በገጠር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ በመተግበር ክትመትን ማሳደግ፤ ከተሞች አሳታፊ እና ዘላቂ ልማትን በሚያቀናጅ ተዋረድ ባለው የተሟላ ዕቅድና ባልተማከለ የከተማ አስተዳደር እንዲመሩ ማድረግ፤ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ በከተሞች የመሬት እና የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አስተዳደር ሥርዓት ውጤታማነት በማሻሻል ምቹ የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር፤ ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ መሠረተ ልማትና የአገልግሎት አቅርቦትን ማሻሻል፤ የከተሞችን ጽዳት አገልግሎት እና የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሽፋንና ተደራሽነትን በማሳደግ ከተሞች ለኑሮ ምቹ እና ተስማሚ እንዲሆኑ ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮሎጂያዊ ተጽዕኖዎች የማይበገሩ ማድረግ ናቸው። በገጠር ማዕከላት የመኖሪያ ቤቶችን ስታንዳርድ ማስያዝ፤ የከተሞችን ኢኮኖሚ በማሳደግ ለኢንዱስትሪ መሰረት የሚጥል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተራፕራይዞች ልማት ሥራዎችን በማስፋፋት ሥራ አጥነትን መቀነስ እንዲሁም በከተሞች

የምግብ ዋስትና ሥርዓትን በማስፋት ድህነትን መቀነስ፤ መልካም አስተዳደር በከተሞች ጥልቀት እንዲያገኝ ማድረግ፤ የከተሞችን የፋይናንስ አቅም፣ አስተዳደርና የሀብት አጠቃቀም በማሻሻል በቂ እና ውጤታማ የከተማ ልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ ተጨማሪ ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የከተሞች ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- 4 ሺህ የሚጠጉ ከተሞች እና 14 ሺህ የገጠር ልማት ማዕከላት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና የአካባቢያዊ ልማቶችና አገልግሎቶች በተቀናጀ የከተሞች ዕቅድ እንዲመሩ ማድረግ፣
- መሬትን በቁጠባ ለመጠቀም እንዲቻል የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና የካዳስተር ሽፋንን ከ3 በመቶ ወደ 60 በመቶ በማሳደግ ከተሞች የመሬት ሀብታቸውን በሚገባ የሚያውቁበትና የሚያስተዳድሩበትን ሥርዓት መዘርጋት፣
- መሬት ለልዩ ልዩ ልማት የሚቀርብበትን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ በጨረታ የሚቀርበውን የመሬት ድርሻ ከ5 በመቶ ወደ 40 በመቶ በማሳደግ እና በመንግስት ምደባ የሚቀርበው ድርሻ ከ95 በመቶ ወደ 60 በመቶ በመቀነስ ከጠቅላላ የከተማ መሬት ፍላጎት ውስጥ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆነው መልስ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- ሁሉም ከተሞች በፕላን መመሬታቸውን በማረጋገጥና የደቀቁ ከተሞችን መልሶ በማልማት የከተማ ፕላንን የማያሟሉ የከተማ ክፍሎችን ምጣኔ ከ74 በመቶ ወደ 30 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣
- ከ4.4 ሚሊዮን በላይ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት የከተሞችን የቤት አቅርቦት ምጣኔ ከ64 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣
- የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች 600 ሺህ (በአጠቃላይ ለመገንባት ከታቀዱት ቤቶች 14 በመቶ) የሚጠጉ የመኖሪያ ቤቶችን መገንባት፣
- የገጠር ማዕከላት የመኖሪያ ቤቶችን ስታንዳርድ በማስያዝ 2.8 ሚሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች የሚገነቡ ሲሆን ቢያንስ 80 በመቶ የሚሆኑ አዳዲስ እና 50 በመቶ የሚሆኑ ነባር ግንባታዎች የጥግግት ስታንዳርድን እንዲያሟሉ ማድረግ፣
- ለከተሞች ልማት የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ፍላጎት ቢያንስ 60 በመቶውን ማሟላት፤ ከዚህም ውስጥ በከተሞች ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች 10 በመቶ በህብረተሰብ መዋጮ እንዲሸፈን ማድረግ፣
- ማዘጋጃ ቤት ያላቸው ከተሞች ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት ከልማት ፋይናንስ ወጪያቸው 60 በመቶውን በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ እና የከተሞች የበጀት አፈጻጸም 95 በመቶ እንዲደርስ ማድረግ፣
- አዲስ አበባና ሌሎች የተሟላ ካዳስተር ሊኖራቸው የሚችሉ 6 ከተሞች ቦንድ ሸጠው በመበደር የመሠረተ ልማት በጀት ክፍተታቸውን እንዲሸፍኑ ማድረግ፣
- የከተሞችን ጽዳት አገልግሎት እና የአረንጓዴ መሰሠተ-ልማት ሽፋንና ተደራሽነትን በማሳደግ ከተሞች ለኑሮ ምቹ እና ተስማሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ከ20 ሺህ በላይ ሕዝብ ባላቸው ከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ምጣኔ ከ1.0 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ የደረቅ ቆሻሻ ሽፋንን ከ30 በመቶ ወደ 80 በመቶ እና በሁሉም ከተሞች ደረጃውን የጠበቀና ተደራሽ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሽፋንን 30 ከመቶ በማድረስ ደረጃውን ያሟሉ ከተሞችን ብዛት ከ6 ወደ 200 ማሳደግ፣

- በከተሞች ለ15 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የከተማ ሥራ አጥነት ምጣኔን ከ18.7 በመቶ ወደ 9 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣
- 2 ሚሊዮን አዳዲስ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንዲፈጠሩ በማድረግና ከዚህም ውስጥ 10 በመቶ የሚሆኑትን ወደ አነስተኛ ደረጃና 1 በመቶ የሚሆኑትን ወደ መካከለኛ ደረጃ ማኑፋክቸሪንግ በማሸጋገር ለኢንዱስትሪ ዕድገት የሚኖራቸውን አስተዋጽዖ ማሳደግ፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ 972 ከተሞች በምግብ ዋስትና ሥርዓት እንዲታቀፉ በማድረግ፤
    - የመሥራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 3.62 ሚሊዮን የከተማ ነዋሪዎች የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች እንዲሳተፉ ማድረግ፣
    - የመሥራት አቅም ለሌላቸውና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ለተጋለጡ በጥቅሉ 689 ሺህ ለሚሆኑ የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአዕምሮ ህሙማንና ህጻናት እንዲሁም 44 ሺህ የጎዳና ተዳዳሪዎች የማህበራዊ ሴፍቲኔት የቀጥታ ድጋፍና መሠረታዊ የማህበራዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ።

# ምዕራፍ ስድስት

## የአስር ዓመቱ
## የመሠረተ ልማት ዕቅድ

# 6.1 የትራንስፖርት ልማት

የትራንስፖርት መሠረተ ልማት አቅርቦትንና የትራንስፖርት አገልግሎትን ማስፋፋት፤ የተሳለጠ የሎጀስቲክ አገልግሎት መስጠት፤ የግል ባለሀብቱ በትራንስፖርት ዘርፍ ላይ የሚያደርገውን ተሳትፎ ማሳደግ እና የዘርፉን የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም ማለትም የሰው ኃይል አደረጃጀቶችን፣ ፖሊሲዎችን፣ የሕግ ማዕቀፎችን እና አሠራሮችን ማጎልበት የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና ዋና ዓላማዎች የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና አገልግሎት ደህንነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ ተደራሽነትንና ጥራትን የጠበቀ ማድረግ፤ የሎጀስቲክስ አገልግሎትን ቀልጣፋና አስተማማኝ ማድረግ፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሠረተ ልማትና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ እና የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም በመገንባት የዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (2013-2022) የትራንስፖርት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የመንገድ ትራንስፖርት መሰረተ ልማት ማስፋፋት፤
    - 102 ሺህ ኪ.ሜ አዲስ መንገድ በመገንባት የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን ከ144 ሺህ ወደ 246 ሺህ ኪ.ሜ ማሳደግ፣
    - 28 ሺህ የነባር መንገዶችን ደረጃ ማሻሻል እና ይዞታ ማጠናከር፣
    - ፍጥነት መንገድ ግንባታን ከ301 ወደ 1650 ኪ.ሜ ማድረስ፣
    - ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ (URRAP) ግንባታ ከ56 ሺህ ወደ 109 ሺህ ኪ.ሜ በማድረስ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መንገዶችን ከ58 ወደ 87 በመቶ ከፍ ማድረግ፤

- የትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋት፤
    - የጭነት ትራንስፖርት ተርሚናሎችን ከ1 ወደ 23 መጨመር፣
    - የደረቅ ወደቦችን ብዛት ከደረሰበት 8 ወደ 11 ማሳደግ፣
    - በጥናት በተለዩ ቦታዎች የቀዝቃዛ መጋዘን በመገንባት ቁጥራቸውን ከ3 ወደ 6 ማሳደግ፤

- የባቡር መሠረተ ልማት ሽፋንን ከ902 ወደ 4,199 ኪ.ሜ ማሳደግ፤
- የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ለማስፋፋት ደረጃቸውን የጠበቁ 6 ኤርፖርቶችን፣ 6 የመንገደኛ ማስተናገጃ ተርሚናሎች እና 10 ጥርጊያ አውሮፕላን ማረፊያዎች መገንባት፤
- የሀገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት መሠረተ ልማት በጣና፣ ባሮ፣ አባያ፣ ጫሞ፣ ህዳሴ ግድብና ጊቤ ወንዝ ላይ በመገንባት የውሃ የትራንስፖርት አገልግሎት ማስጀመር፤
- የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋንን በገጠር ከ67 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ እና የከተማ ብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋንን ድርሻ ከ34 ወደ 70 በመቶ ማሳደግ፤
- ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለንን የሕዝብ ትራንስፖርት ትስስር በመንገድ ትራንስፖርት ብዛቱን ከነበረበት 1 ወደ 6 ማሳደግ፤

- የሀገር አቋራጭ የባቡር ትራንስፖርት የመንገደኛን ቁጥር ከነበረበት 79.19 ወደ 448.6 ሺህ እና የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን በቀን የማጓጓዝ አቅም ከ75 ወደ 200 ሺህ ተሳፋሪ ማሳደግ፤
- የአየር ትራንስፖርትን በተመለከተ ዓለም አቀፍ መንገደኞችን ከ10.2 ወደ 48.4 ሚሊዮን እና የሀገር ውስጥ መንገደኞችን ከ2 ሚሊዮን ወደ 11.8 ሚሊዮን ማሳደግ፤
- በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርስ የሰው ሞት በ10 ሺህ ተሽከርካሪ ከ34.4 ወደ 10 ዝቅ ማድረግ፤
- የሀገሪቱን ገቢና ወጪ ጭነት የማንሳት አቋም ከ17.7 ወደ 30.41 ሚሊዮን ቶን በማሳደግ በዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ አፈጻጸም ደረጃን ከ126ኛ ወደ 40ኛ ማድረስ፤
- ከመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ የሚወጣውን የ14 ሚልዮን ቶን ካርበን ተመጣጣኝ (carbon equivalent) ጋዝ ልቀትን በ13.2 ሚልዮን ቶን በመቀነስ ሊደርስ ከሚችለው 41 ሚሊዮን ወደ 27.8 ሚሊዮን ቶን የካርበን ልቀት ማድረስ፤
- የዘርፉን የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፤
  - የግንባታ ኘሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸምን ከ35 ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣
  - የመንገድ የፈንድ ገቢ አቅምን ከ2.97 ቢሊዮን ወደ 14.2 ቢሊዮን ብር ማሳደግ፣
  - መንገድ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲኖራቸው በማድረግ የመድን ፈንድ ገቢን ከ530.965 ሚሊዮን ወደ 3.2 ቢሊዮን ብር ማድረስ፣
  - በትራንስፖርት ዘርፍ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በዓመት የሚሰበሰብ ገቢን ከ2.39 ቢሊዮን ወደ 7.71 ቢሊዮን ብር ማድረስ፣
  - በመንግስትና የግል አጋርነት የሚተገበሩ 23 ፕሮጀክቶችን ማስጀመር፣
  - በትራንስፖርት ዘርፍ ለ1,425,286 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር።

## 6.2 የውኃ ኃብት ልማት

የውኃ ልማት የንጹህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን፣ የመስኖና እና የተፋሰስ ልማትን ያጠቃልላል። በዚህም የንጹህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማስፋፋት፤ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ተቋማትን አገልግሎት በዘላቂነት እንዲቀጥሉ ማስቻል፤ የታዳሽ ኃይል የመጠጥ ውኃ አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፤ የከተሞች ፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማጠናከርና አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፤ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን ማሳደግ እና ድንበርና ድንበር ተሻጋሪ የውኃ ሀብት ጉዳዮች ፍትሐዊ አጠቃቀምን በማረጋገጥ በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን አቅርቦት ድጋፍ ሥራን ማከናወን፤ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢዎች ወጥነትና ዘላቂነት ያለው ድጋፍ ማድረግ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ።

በተጨማሪም የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ማስፋፋት፤ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፤ ለተማሩና መለስተኛ ሙያ ላላቸው ወጣቶች በዘመናዊ መስኖ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ በመስኖ ልማት ላይ የመንግስት ወጪ ቅነሳና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በማስፋት የመንግስትና የግል አጋርነትን ማጎልበት፤ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው ጊዜና በጀት እንዲሁም በተፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠናቅቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ፤ ተቋማዊ አቅም እና የሰው ኃብት ልማትን ማሳደግ፤ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማደራጀት የጥገና ወጭን እንዲሸፍኑ ማስቻል፤ የስርዓተ ፆታና አካል ጉዳተኞችን አካታችነት ማረጋገጥ እና የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው። የውኃ ልማት ዋና ዋና ዓላማዎች የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን አቅርቦትን ፍትሐዊ፣ ተደራሽ እና ጥራትን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ እና የሀገሪቱን የተፋሰስና የመስኖ ሀብት ማልማት እና አጠቃቀምን ማጎልበት ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት (ከ2013-2022) የውኃ ሀብት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የውኃ ተደራሽነት እና ሽፋንን ማሳደግ፤
    - በገጠር 25 ሊትር ውኃ በሰው በቀን ከ1 ኪ.ሜ ባልበለጠ ርቀት በማዳረስ የውኃ ሽፋኑን ከ54.88 ወደ 100 በመቶ ማድረስና ከዚህም መካከል 50 በመቶ የቧንቧ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣
    - የከተማ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን አገልግሎትን 100 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 1፣ 80 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 2፣ 60 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 3፣ 50 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 4 እና 40 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 5 ከተሞች በማቅረብ ሽፋኑን ከ58.9 ወደ 100 በመቶ ማድረስና ሁሉም የቧንቧ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
    - ድርቅ በተደጋጋሚ በሚያጠቃቸው 100 ወረዳዎች የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም የባለ ብዙ መንደሮች የመጠጥ ውኃ ማቅረብ፤

- በ100 ከተሞች መሠረታዊ የተቀናጀ የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት እና ሁሉም የገጠር መንደሮች የመፀዳጃ ቤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ለሁሉም የትምህርትና የጤና ተቋማት የንጹህ የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አገልግሎትን ማዳረስ፤
- የውኃ ብክነትን መጠን ከ39 ወደ 20 በመቶ ዝቅ ማድረግ፤
- በፍሎራይድ የተበከለ ውኃ ተጠቃሚ የሆነውን ነዋሪ ቁጥር ከ3.5 ሚሊዮን ወደ 0 ሚሊዮን መቀነስ፤
- የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሽፋንን ከ2.25 ሚሊዮን ወደ 10 ሚሊዮን ሄክታር ማድረስ፣ የኢኮ-ሀይድሮሎጂ ሰርቶ ማሳያዎችን ቁጥር ከ10 ወደ 55 ከፍ ማድረግ፣ በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ ላይ የሀገራችንን ጥቅም ሙሉ በሙሉ ማስጠበቅ እና የገጸ ምድር ውኃ ሀብት የፍሰት መረጃ ከ78 ወደ 100 በመቶ ማድረስ እንዲሁም የከርሰ ምድር ውኃ ሀብት መረጃ ሽፋንን ከ17.95 ወደ 35 ከፍ ማድረግ፤
- የመካከለኛ ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ጥናትና ዲዛይን ከ600 ሺህ ወደ 2 ሚሊዮን ሄክታር እና የመካከለኛ ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ግንባታ ከ490 ሺህ ወደ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ፤

- የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ከ2 ወደ 20 በመቶ ማሳደግ፤
- በ20 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች የውኃ አጠቃቀም ውጤታማነትን ከ30 ወደ 50 በመቶ እንዲሁም የሚለማ መሬት መጠቀምን መጠን ከ33 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- የመስኖ አውታርን በማስፋት ለዜጎች 820 ሺህ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ በመስኖ መሠረተ ልማት ጥገና፣ ግንባታ እና ተዛማጅ ሥራዎች ለወጣቶች 110 ሺህ እንዲሁም ለተማሩ ወጣቶች 120 ሺህ የሥራ ዕድል መፍጠር።

## 6.3 የኢነርጂ ዘርፍ ልማት

ኢነርጂ ዘርፍ ልማት የኢነርጂ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ ንጹህ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ለገጠሩ ህብረተሰብ ማዳረስ፣ ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ማቅረብ፣ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል መሠረተ ልማት መገንባት፣ ጤናማ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋም እንዲኖር ማድረግ፣ ባለሃብቶች በዘርፉ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈሱ ማበረታታት እና ብቃትና ሥነ ምግባር የተላበሰ የሰው ኃይል መፍጠር የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የኢነርጂ ዘርፍ ዋና ዋና አላማዎች ተደራሽ፣ጥራቱን የጠበቀ፣ አቅምን ያገናዘበ፣ ፍትሐዊ እና ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ማቅረብ እና አስተማማኝ የኢነርጂ መሰረተ ልማት ማስፋፋት ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (ከ2013-2022) የኢነርጂ ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅምን ከ4,478 ሜጋ ዋት ወደ 19,900 ሜጋ ዋት ማድረስ፤
- የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሩን ርዝመት በ18,400 ወደ 29,900 ኪ.ሜ ማድረስ፤
- የኢነርጂ የወጭ ንግድ መጠንን ከ2,803 ወደ 7,184 ጊጋ ዋት በሰዓት (GWH) ማሳደግ፤
- የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞችን ከ5.8 ሚሊዮን ወደ 24.3 ሚሊዮን ማሳደግ፤
- የግሪድ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎችን ከ33 ወደ 96 በመቶ እንዲሁም ከግሪድ ውጭ ተጠቃሚ የሆኑ ድንበኞችን ቁጥር ከ11 ወደ 4 በመቶ መቀነስ፤
- የኤሌክትሪክ ብክነትን ከ19.6 ወደ 12.5 በመቶ መቀነስ።

# 6.4 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ልማት

ለኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት የሚውሉ መሠረተ ልማቶችን መገንባት እና ማደራጀት፤ የሠው ኃብት አቅምን መገንባት፤ ወሳኝ የሆኑ ተቋማትን ማቋቋም፣ መደገፍና ማብቃት እንዲሁም የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት፤ ሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን በማከናወን ረገድ ሀገራዊ የዳታ ማዕከል መገንባት፤ የተቋማትን የኢንተርኔት ትስስር ሽፋንና የመጠቀም ደረጃ በማሻሻል በቀጥታ በበይነ መረብ (online) የሚሰጡ የመንግስት አገልግሎቶችን ማሳደግ፤ ሀገር አቀፍ የአድራሻ ሥርዓት መዘርጋት፤ ኮምፒዩውቴሽናል ቴክኖሎጂዎችን እና ብሔራዊ የዳታ ክምችቶችን ማልማት እና የመንግስት አገልግሎቶችን ተገልጋዮች በኤሌክትሮኒክ አግባብ እንዲያገኙ ትኩረት መስጠት የዘርፉ ዓላማዎች ናቸው።

የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ልማት ዋና ዋና ዓላማዎች የሀገራዊ የኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ አቅምን መገንባት፤ የዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤ የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል እና የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ የሬጉላቶሪና የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት፤
    - የህዋ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሊያዘምኑ የሚችሉ 9 የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ሥራዎችን ለማጠናከር የሚያስችሉ 20 አዳዲስ የኢንኩቤሽን ማዕካለት እና 8 የቴክኖሎጂ ማዕከላትን መገንባት፣
    - የኒውክሌር ፍንዳታ እገዳ ስምምነትን ለማስፈጸም የሚያስችል አንድ የራዲዮ ኒውክላይድ ጣቢያና 50 ያለማቋረጥ ከሳተላይት መረጃ የሚቀበሉ ጣቢያዎች መገንባት፣
    - 450 መሠረታዊ (Zero Order) የምድር መረጃ መቆጣጠሪያ ነጥቦች፣ 1000 አንደኛ ደረጃ (1st order) የምድር መረጃ መቆጣጠሪያ ነጥቦች፣ 1 የጂኦስፓሻል ላብራቶሪ እና 1 የጂኦስፓሻል ሰርቨር ሩም መገንባት፤
- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አቅም መገንባት እና አገልግሎት አሰጣጥን ማጎልበት፤
    - በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂና ምርምር ዘርፍ ሊሰማራ የሚችለውን የሰው ሀብት አቅም በመገንባት ወደ 5.7 ሚሊዮን ማድረስ፣
    - የብሔራዊ የዳታ ማዕከሎችን ብዛት ካለበት 1 ወደ 3 ማድረስ፣
    - የአድራሻ ሥርዓት የሚጠቀሙ ከተሞችን ብዛት ወደ 73 ማድረስ፣

- በመንግስት ኔትውርክ ውስጥ የሚካተቱ የመንግስት ተቋማትን ሽፋን ወደ 95 በመቶ ማድረስ፣ 2 የሪሞት ሴንሲንግና 1 የኮሚዩኒኬሽን ሳታላይቶች ማምጠቅ፣
- በኤሌክትሮኒክ የሚሰጡ የመንግስት አገልግሎቶችን ከ176 ወደ 2,500 ማድረስ፣
- የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን ሽፋን ከ2 በመቶ ወደ 85 በመቶ በማሳደግ የኤሌክትሮኒክ ግብይት አገልግሎትን የሚጠቀሙ ተቋማትን ብዛት 3,500 ማድረስ፤

- የሞባይልና የኢንተርኔት ተጠቃሚዎችን ተደራሽነት በቅደም ተከተል ከ37.2 እና ከ18.6 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤

- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት እና ማጎልበት፤

  - የሳተላይት መረጃዎችን በማጎልበትና በማሰራጨት መስክ 20 ኢንተርፕራይዞችን እንዲሁም የስፔስ ቴክኖሎጂዎችን ማልማት፣
  - በማላመድና በማሸጋገር መስኮች 36 ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋም፣
  - 50 የተለያዩ የቴክኖሎጂ ስታርትአፕና የፈጠራ ውጤቶች ያላቸውን ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች ወደ ምርትና አገልግሎት አቅርቦት እንዲገቡ ማድረግ፣
  - ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ ለሆኑ ለ3,000 የተመረጡ የቴክስታርትአፖች ድጋፍ በማድረግ 2,100 የሚሆኑትን ማሸጋገር፣
  - በቴክኖሎጂና ዲጂታላይዜሽን ኢንዱስትሪው የግሉ ዘርፍ የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል ሽፋን ከደረሰበት 50 ወደ 80 በመቶ ማሳደግ።

# ምዕራፍ ሰባት

## የአስር ዓመቱ የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

# 7.1 የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት

በቀጣይ አስር ዓመታት በሥነ-ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት ዋና የትኩረት አቅጣጫ አሁን በትግበራ ላይ ባለው የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ የተቀመጡ ዓላማዎችን እና በቀጣይ ፖሊሲውን ከመከለስ ጋር ተያይዞ የሚካተቱ አዳዲስ ዓላማዎችን ውጤታማ በሆነ አግባብ ተፈጻሚ ለማድረግ ማስቻል ነው።

ከዚህ አኳያ በቀጣይ በአጠቃላይ ኢኮኖሚ በተለይም በሠው ሀብት ልማት ዙሪያ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ የሥነ ሕዝብ ሽግግርን ማፋጠን እና የሥነ ሕዝብ ትሩፋትን አዎንታዊ በሆነ አግባብ መጠቀም፤ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲና ፕሮግራሞችን የሚያስፈጽሙና የሚተገብሩ የፌደራል የዘርፍ አስፈጻሚ አካላት የሚመለከታቸውን የሥነ ሕዝብ ተግባራት የዘርፍ ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሩ ማስቻል፤ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፤ የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ እንዲሁም ውጤታማነት እንዲጎለብት ማድረግ፤ ወቅታዊ የሥነ ሕዝብ መረጃዎችን ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ ከገጠር ወደ ከተማ እንዲሁም ከትናንሽ ወደ ትላልቅ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰት ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል እና የአካባቢ ደህንነት እንዲሻሻል የሚመለከታቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች በተቀናጀ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት ዋና ዋና ዓላማዎች ሁለንተናዊ የሰው ሀብት አቅምን ይበልጥ ለማዳበር የጤናና የትምህርት ፍትሃዊ ተደራሽነትን፣ ጥራትንና አግባብነትን ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በቀጣይ አስር ዓመታት በነዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። ይህ ዓላማ የዜጎችን ሰብዓዊ ፍላጎት ከማረጋገጥ አንጻር በራሱ በቂ ቢሆንም ሀገራት ጤነኛና የተማሩ ዜጎች ሲኖራቸው ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። ስለሆነም የልማት ዕቅዱ ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋና ዓላማዎች ተቀምጠዋል።

በሽታ መከላከል ላይ ያተኮረ የማይበገር የጤና ሥርዓት በመገንባት የእናቶችንና የህጻናትን ሞት መግታት፤ ተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ሳቢያ የሚደርስ ህመምና ሞትን መከላከልና መቀነስ እና ዜጎችን ከድንገተኛ የጤና አደጋዎች መጠበቅ።

ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጨረሻ ድረስ ለዜጎች ጥራት ያለው ነጻ ትምህርት በፍትሃዊነት ማዳረስ፤ የትምህርት ውጤቶችን ማሻሻል፤ የትምህርትና ስልጠና ጥራትን እና የምዘና ሥርዓትን አጠናክሮ ማስቀጠል፤ ሥርዓተ ትምህርትን፣ የመማር ማስተማር ሂደትን፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችንና የመገምገሚያ ሥርዓቱን ተገቢነት ማረጋገጥ፤ ዜጎች የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና በቅርበት ሊያገኙ የሚችሉበትን እና በሚመርጧቸው የትምህርት መስኮች የመግባት እድልን ማስፋት፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በስነ ልቦና፣ በሙያ፣ በአእምሮ፣ በመንፈስ፣ በአካልና በማሕበራዊ እድገቱ የዳበረ ሀገርንና ወገንን የሚወድና የሚያከብር ምሩቅ እንዲያወጡ ማስቻል፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠናውን የኢኮኖሚውን የሙያና የሥራ ፍላጎት ያማከለና ያስተሳሰረ ማድረግና የሀገር በቀል እውቀቶችን ማልማት፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በጥንካሬያቸውና በአካባቢያቸው ያለውን እምቅ ሀብት በመለየት እንደየትኩረት መስካቸው አቅማቸውን ማጎልበት፤ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና በኢንዱስትሪ መካከል የሥራ ትስስር መፍጠርና ማጠናከር፤ በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማሳደግ፣ ማስፋፋትና ማጠናከር።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የቤተሰብ ዕቅድ ስርጭት ምጣኔን ከ41 በመቶ ወደ 54 በመቶ ማሳደግ፤
- የህዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔን በአማካይ ወደ 2.0 በመቶ መቀነስ፤
    - የከተማና የገጠር የሕዝብ ብዛት የዕድገት ምጣኔ በቅደም ተከተል 4.2 በመቶ እና 1.3 በመቶ ማድረስ፣
    - የከተሜነት ምጣኔ ከ21.4 በመቶ ወደ 35 በመቶ ማድረስ፣
    - ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት የኢኮኖሚ ጥገኝነት ምጣኔ ከ68 በመቶ ወደ 59 በመቶ ማድረስ፤
- የእናቶችን ሞት ምጣኔ በ2009 በጀት ዓመት ከነበረበት 401/100,000 በ2022 ወደ 140/100,000 መቀነስ፤
- ከ5 ዓመት እና ከ1 ዓመት እድሜ በታች ያሉ የህጻናትን በተመለከተ፤
    - ከ5 ዓመት እና ከ1 ዓመት በታች ያሉ ህጻናትን ሞት ምጣኔ በቅደም ተከተል ከ59/1,000 ወደ 37/1,000 እና ከ47/1,000 ወደ 29/1,000 መቀነስ፣
    - ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናትን የመቀንጨርና የመቀጨጭ ምጣኔ በቅደም ተከተል ከ37 በመቶ ወደ 13 በመቶና ከ7 በመቶ ወደ 3 በመቶ መቀነስ፤
- በቲቢና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ የሚደርሰውን የሞት ምጣኔ በቅደም ተከተል ከ22/100,000 ወደ 4/100,000 እና ከ1.2/10,000 ወደ 0.45/10,000 መቀነስ፤
- በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስና በወባ በሽታ አዲስ የሚያዙ ሰዎችን ምጣኔም በቅደም ተከተል ከ1.6/10,000 ወደ 0.6/10,000 እና ከ28/1,000 ወደ ዜሮ ማውረድ፤
- በመውለድ ዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሴቶች የሚከሰትን የደም ማነስ በሽታ ምጣኔ ከ24 በመቶ ወደ 12 በመቶ መቀነስ፤
- የጤና ባለሙያ ለ1000 ተገልጋዮች ጥምርታን ከ1.0 ወደ 4.5 እና ሐኪም ለ10,000 ተገልጋዮች ጥመርታን ከ0.86 ወደ 2.7 ማሳደግ፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ለ100,000 ህዝብ ጥምርታን ከ0.3 ወደ 0.85 ማሳደግ፤
- በማህበረሰብ ጤና መድህን ሥርዓት የታቀፉ ቤተሰቦችን ሽፋን ከ49 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- አማካይ የመኖር ዕድሜ ጣሪያን በ2011 ከደረሰበት 65.5 ዓመት በ2022 ወደ 70 ዓመት ማሳደግ፤
- ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ተደራሽነት በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 41.8 በመቶ በ2022 በሁለቱም ጾታዎች ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- ከ1ኛ-6ኛ ክፍል (አማራጭን ጨምሮ) ንጥር የትምህርት ተሳትፎን ከ100.2 በመቶ በሁለቱም ጾታዎች ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ተደራሽነትን ከ97.4 በመቶ በሁለቱም ጾታዎች ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤

- ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎን ከ25.3 በመቶ በሁለቱም ጾታዎች ወደ 75 በመቶ ማሳደግ፤
- መጠነ ማቋረጥ ምጣኔን በ1ኛ ክፍል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 25 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1 በመቶ እንዲሁም ከ7ኛ -8ኛ ክፍል በተማሳይ ዓመት ከነበረበት 12 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ መቀነስ፣
- 8ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔን በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 62.1 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣
- የሴቶችንና የወንዶችን የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ልዩነትን በቅድመ አንደኛ ትምህርት፣ ከ1-6ኛ ክፍል እና ከ7-8ኛ ክፍል በቅደም ተከተል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 1፡0.95 ፤ 1፡0.91 እና 1፡ 0.94 በ2022 በጀት ዓመት በሁሉም ደረጃዎች ወደ 1:1 ለማድረስ እንዲሁም ከ9-12ኛ ክፍል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 0.87፡1 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1፡0.96 ለማድረስ ግብ ተጥሏል።
- የሴት መምህራን ድርሻን በአንደኛ ደረጃ በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 40.6 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 50 በመቶ ለማድረስ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከ19.3 በመቶ ወደ 30 በመቶ ለማድረስ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎን በከ1-8ኛ ክፍል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት2.8 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ዓመት ወደ 50 በመቶ ማድረስ፤
- የአርብቶ አደር ተማሪዎችን ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት ከ13.4 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 92 በመቶ እንዲሁም የአርብቶ አደር ተማሪዎች ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎን ከ74.2 ወደ 96 በመቶ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ትምህርት ንጥር ተሳትፎን ከ16.8 በመቶ ወደ 75 በመቶ፣ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎን ከ14 በመቶ ወደ 60 በመቶ ከፍ ማድረግ፤
- በ6ኛ እና በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና እና በ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና ከዚያ በላይ አምጥተው የሚያልፉ ተማሪዎች በ2022 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል ወደ 100፣ 100 እና 95 በመቶ ማድረስ፤
- ደረጃ 4 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛት በቅድመ መደበኛ፣ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ በቅደም ተከተል ከ0 ወደ 30 በመቶ፣ ከ0.01 ወደ 30 በመቶ እና ከ0.1 ወደ 30 በመቶ ማድረስ፤
- ደረጃ 3 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛት በቅድመ መደበኛ ከ5 ወደ 70 በመቶ፣ በአንደኛ ደረጃ ከ11 ወደ 70 በመቶ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከ11 ወደ 70 በመቶ ማድረስ፤
- የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች አመታዊ ጥቅል ቅበላ ከ13.8 በመቶ ወደ 23 በመቶ ማድረስ፤
- የመንግስት እና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅደም ተከተል ከ45 እና 238 ወደ 55 እና 550 ማድረስ፤
- የመንግስት እና የግል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት በቅደም ተከተል ከ672 ወደ 922 እና ከ950 ወደ 1700 ማሳደግ፤
- በዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተሳትፎ ከ0.29 ወደ 5 በመቶ፣ በዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከ35.9 ወደ 48 በመቶ እንዲሁም በበቴክኒክና ሙያ የሴት መደበኛ ሰልጣኞች ተሳትፎ ከ49.8 ወደ 51 በመቶ ማድረስ፤
- በሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ በተመሳሳይ ዓመታት በቅደም ተከተል ከ19 እና 10 በመቶ ወደ 35ና 23.4 በመቶ ማድረስ፤
- በዩኒቨርሲቲ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከ30.7 በመቶ ወደ 40 በመቶ፣ በቴክኒክና ሙያ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ተሳትፎ በመደበኛ ከ1365 ወደ 1443 ማድረስ፤

- የመምህር - ተማሪ ጥምርታን በመጀመሪያ ዲግሪ አሁን ካለበት ከ1፡19 ወደ 1፡15፣ በድህረ - ምረቃ ከ1፡ 20 ወደ 1፡5 ማውረድ፤
- በኢንደስትሪው ባለቤትነት የተዘጋጀ የሙያ ደረጃ ከ750 ወደ 850 ማሳደግ፤
- በኢንደስትሪ ፍላጎት መሰረት የተከለሰ ዩኒቨርሲቲዎች የሙያ ፕሮግራሞች ብዛት ከ282 ወደ 512 ማሳደግ፤
- በግብዓት የተሟሉ ቤተ ሙከራዎች ያሏቸው የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን እና ዩኒቨርሲቲዎችን በቅደም ተከተል ከ40 ወደ 100 በመቶ እና ከ65.3 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- የቴክኒክና ሙያን በተመለከተ ሰልጣኞች ዓመታዊ መደበኛ መርሃ - ግብር ቅበላን ከ45 ወደ 80 በመቶ፣ የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች የመቀጠር ምጣኔን ከ78 ወደ 96 በመቶ፣ በቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞች መብቃት ድምር ምጣኔን ከ55 ወደ 85 በመቶ፣ በየቴክኒክና ሙያ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰልጣኞች የትምህርትና ስልጠና መብቃት ምጣኔን ከ40 ወደ 70 በመቶ፣ በበቴክኒክና ሙያ የሴቶች ሰልጣኞች መብቃት ምጣኔን ከ45 ወደ 75 በመቶ ማሳደግ፤
- የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በተመለከተ የሴት ተመራማሪዎችን ድርሻ ከ16.4 ወደ 40 በመቶ፣ የበጀት መጠን እድገትን 40 በመቶ፣ የመንግስት የቅድመ - ምረቃ ተማሪዎችን የመመረቅ ምጣኔ አጠቃላይ ከ84.2 በመቶ ወደ 92.5 በመቶ፣ በዩኒቨርሲቲ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የማጠናቀቅ ምጣኔ ከ89.14 በመቶ ወደ 95 በመቶ፤ በዩኒቨርሲቲ የሴቶችን የማጠናቀቅ ምጣኔ 74.04 በመቶ ወደ 90 በመቶ፤ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ተማሪዎችን ምረቃ ምጣኔ ከ94.5 በመቶ ወደ 97 በመቶ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተማራቂዎች የመቀጠርን ምጣኔ ከ59 ወደ 90 በመቶ ማሳደግ።

## 7.2 የማህበራዊ ፍትህ እና ዋስትና ልማት

በቀጣይ አስር ዓመታት በማህበራዊ ፍትህ እና ዋስትና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የዜጎችን ፍትሃዊ የልማት ተሳትፎ ሚናና ተጠቃሚነት በዘላቂነት እንዲረጋገጥ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በክህሎት የታነፁ እንዲሆኑና የተገነባ አቅም እንዲኖራቸው ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በተለይ የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የወጣቶችን የአረጋዊያንን፣ የአካል ጉዳተኞችን እና ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን አጠቃላይ የማህበራዊ ዋስትና ሥርዓት በማጠናከር ሁለንተናዊ ደህንነታቸውን የማስጠበቅና መብታቸውን የማስከበር፤ በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ፍትሃዊ ተሳትፎ እና ውክልና እንዲኖራቸው የማድረግ እና በኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዘርፎች ላይ ያላቸውን ሚና እንዲያጎለብቱ በማድረግ ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የዘርፉ ልማት ዕቅዱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የማህበራዊ ፍትህ እና ዋስትና ልማት ዋና ዋና ዓላማዎች የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋዊያንን፣ የአካል ጉዳተኞችን እና ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን ሁለንተናዊ ብቃት በማሳደግ በሀገሪቱ በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተደራጀና በተቀናጀ አኳኋን የነቃና ግንባር ቀደም ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከውጤቱም በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የማህበራዊ ፍትህ እና ዋስትና ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

- የህፃናትን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ እንዲሁም ተሳትፎንና ውክልናን ማረጋገጥ፤
    - በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 15 ሚሊዮን ህፃናትን መደገፍ፣
    - የህፃናት ልደት ምዝገባ ተደራሽነትን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣
    - ለህፃናት ተሳትፎ አዎንታዊ አመለካከት ያለውን ህብረተሰብ 80 በመቶ ማድረስ፣
    - የህፃናት ፓርላማ አደረጃጀቶችን ከ8,428 ወደ 20,015 ማሳደግ፣
    - በህፃናት ፓርላማዎች ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ ህፃናትን ድርሻ 75 በመቶ ማሳደግ፣
    - በስብዕና ማዕከላት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን 50 በመቶ፤ በህፃናት ማቆያ ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን 70 በመቶ፤ ለትምህርታቸው፣ ለራሳቸውና ለብዝሀነት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸውን ህፃናት 95 በመቶ፤ ከቤተሰብና ከማህበረሰባቸው ጤናማ ግንኙነት ያላቸውን ህፃናት 90 በመቶ ማድረስ፤

- የሴቶችን ደህንነት ማስጠበቅና መብታቸውን ማስከበር፣ ተሳትፎና ውክልና እንዲሁም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤
    - ለአካላዊ ጥቃት የተጋለጡ ሴቶችን ምጣኔ ስነ-ልቦናዊ ጥቃት (emotional attack) በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት 24 በመቶ፣ የሴት ልጅ ግርዛትን ከነበረበት 65 በመቶ እና ያለዕድሜ ጋብቻን ከነበረበት 6 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ፣
    - ለወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ ሴቶችን ምጣኔ ከነበረበት 10 በመቶ ወደ 5 በመቶ መቀነስ፤
    - ኢትዮጵያን የአፍሪካ የሴቶች አመራር ማዕከል በማድረግ ለአመራር ብቁ የሆኑ 10,000 ሴቶችን ማፍራት፣
    - የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ድርሻ በህግ አውጪ 50 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ 50 በመቶ፣ በህግ አስፈፃሚ አሁን ያለውን የ50 በመቶ ድርሻ ማስቀጠል፣
    - የሴቶች የሥራ ክፍያ ከወንዶች አንጻር ያለውን ልዩነት ከ44 በመቶ ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት፣
    - የመሬት ባለቤትነትን መብት ካላገኙ ሴቶች ውስጥ 59.7 በመቶ ያህሉን የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጥ፣
    - በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ምጣኔ ከ41 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፣
    - ብድር አግኝተው በገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተሳተፉ ሴቶችን መጠን ከ33 በመቶ ወደ 55 በመቶ ማሳደግ፤

- የወጣቶችን መብት፣ ተሳትፎና ውክልና እንዲሁም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
    - በህግ አውጪ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችን ከ11 በመቶ ወደ 30 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ ከ10.2 በመቶ ወደ 35 በመቶ እንዲሁም በህግ አስፈፃሚ ከ12.2 በመቶ ወደ 30 በመቶ ማሳደግ፣

- የብድር አገልግሎት ያገኙ ወጣቶችን ከ25 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ የቁጠባ ምጣኔያቸው ያደገ ወጣቶችን ከ7 በመቶ ወደ 15 በመቶ ማሳደግ፤

- የሠራተኞችን መብትና ማህበራዊ ዋስትና እንዲሁም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
    - የአሠሪዎችንና የሠራተኞችን በነፃ የመደራጀት ምጣኔ ማሳደግ፣
    - የአሠሪዎች በማህበር የመደራጅት ምጣኔን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ2.5 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 20 በመቶ ለማሳደግ፣ የሠራተኞች በማህበር የመደራጀት ምጣኔን ከ2 በመቶ ወደ15 በመቶ ለማሳደግ፣
    - በድርጅቶች የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ሽፋንን ከ372,245 ወደ 838,551 ማሳደግ፣
    - በሥራ ላይ የሚደርሱ የሞት አደጋዎችን ከ52/100,000 ሠራተኞች ወደ 35/100,000 ሠራተኞች መቀነስ፣
    - በሥራ ላይ ሞት ያላደረሱ አደጋዎች ከ25,000/100,000 ሠራተኞች ወደ 10,000/100,000 ሠራተኞች መቀነስ፣
    - አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ከ23 በመቶ ወደ ዜሮ ማውረድ፣
    - የሥራ ስምሪት ድጋፍ አግኝተው በሥራ ላይ የሚሰማሩ ዜጎችን ቁጥር ከ1.96 ሚሊዮን ወደ 20 ሚሊዮን ማሳደግ፣
    - በሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል መረጃ አሰባሰብ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ካለበት ከ50 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 100 በመቶ በማድረስ የመረጃ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ፣
    - በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከሚችሉ ከድህነት ወለል በታች ከሚገኙ አረጋዊያን መካከል 563,640፣ ከአካል ጉዳተኞች መካከል 323,000 እና ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ ከሆኑ የህረተሰብ ክፍሎች (urban destitute) መካከል 189,000 የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት እድል እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዷል።
    - የአካል ድጋፍና ሌሎች አገልግሎቶች የሚደረግላቸው አካል ጉዳተኞች ቁጥርን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 412,867 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 659,558 ለማሳደግ ታቅዷል።
    - የግል ድርጅት ሠራተኞችን የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ምዝገባ ከ1.7 ሚሊዮን ወደ 3.1 ሚሊዮን ማሳደግ፣
    - የግል ድርጅቶችን ምዝገባ አሁን ካለበት ከ203,458 ወደ 311,887 ለማሳደግ፣
    - የጡረታ መዋጮ ገቢን ከ43.9 ቢሊዮን ብር ወደ 231 ቢሊዮን ብር ማሳደግ፣
    - የጡረታ ፈንዱን በኢንቨስትመንት ላይ በማዋል ትርፋን ከ1.4 ቢሊዮን ብር ወደ 39 ቢሊዮን ብር ማሳደግ፣

# ምዕራፍ ስምንት

## የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና
## የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕቅድ

በቀጣይ አስር ዓመታት የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የህዝብ አገልግሎት ሥርዓት መገንባት፣ አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን፣ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፣ የዳኝነት ተደራሽነትን ማስፋፋት፣ የፍርድ ቤት ነጻነትና ተጠያቂነትን ማጎልበት፣ የወንጀል ሕግን አፈጻጸም ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ በየደረጃው ያሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን ሕግ የማውጣትና የመቆጣጠር አቅምን ማሳደግ፤ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት በግልጸኝነትና በተጠያቂነት መርህ መሥራታቸውን ማረጋገጥ፤ ሕግ አውጪው እና ሕግ አስፈጻሚው በሕገ መንግስትና ሕጎች መሠረት በግልጽ የስልጣን ክፍፍል መሥራት የሚያስችላቸው ቁመና መፍጠር፤ ሲቪክ ማህበራት በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ በሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እንዲሁም በማህበራዊ ዘርፎች ላይ ተሳታፊነታቸውን ማጠናከር፤ የዜጎች የመምረጥ እና የመመረጥ መብታቸውን ማረጋገጥ፤ ነጻ እና ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋማትን ማጠናከር ናቸው።

በተጨማሪም መገናኛ ብዙሀን ለመሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች እንዲሁም ለሠላም፣ ለእኩልነት፣ ለፍትሕ እና ለዴሞክራሲ እንዲቆሙ በአጠቃላይ ለልማት እና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የድርሻቸውን መወጣት ይችሉ ዘንድ ከመንግስት እና ከፖለቲካ ፓርቲ ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሁም ተፎካካሪ ሆነው ሊሰሩ የሚችሉበትን ምህዳር መፍጠር፤ የህዝብ ተሳትፎን የስልጣን ባለቤትነት የማረጋገጥ እና የአሠራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሠፈነበት የመንግስት አሠራርና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር፤ ለሙስና ወንጀል የሚያጋልጡ አሠራሮችንና የሕግ ክፍተቶችን በመለየት የመንግስትም ይሁን የግል ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ፣ የሙስና ወንጀል ፈጽመው በተገኙ አካላት ላይ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ እና ለህብረተሰቡ በሚዲያ የማጋለጥ ሥራ መሥራት፣ የክልል የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች የመፈጸም አቅም መገንባትና ተልዕኮ ተኮር የህብረተሰብ ተሳትፎን በማሳደግ የፀረ ሙስና ትግሉ ተባባሪና አጋር አካላትን ማብዛት ሌሎች የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዋና ዋና ዓላማዎች ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የህዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት ማጎልበትና በህዝ አገልግሎት አሠጣጥ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ፤ ፍርድ ቤት እና ዳኞች ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች አካላትና ግለሰቦች ከሚደርስባቸው ማናቸውም ጫና እና ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ በማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የፍርድ ቤት አገልግሎቶችን በእኩልነት እንዲያገኙ ማስቻል፣ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤ የዴሞክራሲ ተቋማትን እና የዜጎችን አመለካከት መቅረጽ ላይ ወሣኝ ሚና ያላቸውን ተቋማት አቅም መገንባት፣ የሙስና ወንጀልን መከላከል፣ በሰላም፣ በልማት እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ወቅታዊ እና ተዓማኒ ዜናና ዜና ነክ ሥራዎችን ማሠራጨት ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- ገለልተኛና ብቁ ተቋማትንና መስፈርቶችን አሟልተው የተፈጠሩ የተቋማት አደረጃጀቶችን ወደ 100 በመቶ ማድረስ፤
- በዘርፉ ያለውን ውጤታማ አምራች የሰው ኃይል ምጣኔ ከ20 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማድረስ፤ የሰው ሀብት የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ስርዓቱን አሟልተው የተገበሩ የፌዴራል ተቋማትን ብዛት ወደ 100 በመቶ ማድረስ እና በመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ የዜጎች እርካታ ከ59 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማድረስ፤

- ደረጃቸውን የጠበቁ የሥራ ቦታዎች የፈጠሩ የፌዴራል ተቋማትን መጠን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤ በመንግስት ተቋማት የሴትና ወንድ አመራር እና ባለሙያዎች ጥምርታን ወደ 36 በመቶ ማሳደግ፤ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የህጻናት ማቆያ ለማዘጋጀት እና ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቸ የሥራ ቦታ መፍጠር፤ 50 በመቶ የሚሆኑ አዳዲስ ተመራቂ ወጣቶችን ወደ ሥራ ማስገባትና በፍጥነት ማሳደግ፤
- የወንጀል ጉዳዮችን የማጥራት ምጣኔ አሁን ካለበት ከ80 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤ የእርቅ ምጣኔ ከ81.2 ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፤ የመንጠባጠብ ምጣኔ ከ1.9 ወደ 0.5 በመቶ መቀነስ፤
- የቅጣት አፈጻጸምን ከ91.8 ወደ 98 በመቶ ማሳደግ እና ከሀገር ውጪ ካለና በወንጀል ከተገኘ ሐብት ውስጥ 59 በመቶውን ማስመለስ፤
- ደረጃውን የጠበቀ ምላሽ ያገኙ የውል ምርመራ ዝግጅት ሥራን ወደ 98 በመቶ ማሳደግ፤ የሕግ ማርቀቅ፣ ምክርና እርማት ምጣኔ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤ በሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ዓለምአቀፍ ትብብር አፈጻጸምን ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፤ ለሚቀርቡ የይቅርታ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ሥራን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤ የይቅርታ ውሳኔዎችን የማጸደቅ ሥራን ወደ 98 በመቶ ማሳደግ፤
- የፍትሐብሔር ፍርድ አፈጻጸም ምጣኔን ከ50 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤ የፍትሐብሔር ጉዳዮች በድርድር የመፍታት አቅምን ከ70 ወደ 92 በመቶ ማሳደግ፤ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ የተደረጉ ሰዎችን መጠን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ፣ እድሳት እና ስነ-ምግባር ክትትል አፈጻጸምን 100 በመቶ ማድረስ፣ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ጠቋሚዎች እና ምስክሮች አገልግሎት ከ61.1 ወደ 79 በመቶ ማሳደግ፤
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥን ወደ 100 በመቶ ማድረስ፤
- ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን አፈጻጸም ክትትል 100 በመቶ ማድረስ፤
- የዜጎች ንቃተ ሕግ ትምህርት ተደራሽነትን ወደ 85 በመቶ ማሳደግ እና የሕግ ድጋፍ ያገኙ ሴቶችና ህፃናትን መጠን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፤
- በየደረጃው ያሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን ሕግ የማውጣትና የመቆጣጠር አቅምን በማሳደግ የተጠያቂነትና የግልፀኝነት ሥርዓት ማረጋገጥ፣ የሀገራችን መገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ተአማኒነትና ተጽዕኖ ፈጣሪነትን ከ20 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፥ የመገናኛ ብዙኃን የምርትና አገልግሎት ጥራት፣ ቅልጥፍናን ከ30 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሣደግ፣

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የሠላም ግንባታ እና

## ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዕቅድ

በቀጣይ አስር ዓመታት ቀጠናዊ የጋራ ልማትን ለማሳደግ በአካባቢያችን ዘላቂ ሰላም፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስርና የጋራ ብልጽግና ለማምጣት የሚያስችል መሪ ስትራቴጂ (grand strategy) ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ በልማት ዕቅዱ ውስጥ እንደ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ተቀምጧል። የአፍሪካ ህብረት ውጤታማ አህጉራዊ ውህደት እንዲያሳካ እንደ አባል እና አስተናጋጅ ሀገር መደገፍ እና ድርጅቱ የሀገራችን ባለብዙ ወገን ድጋፍ መነሻ ሆኖ እንዲቀጥል ብዙ ሥራ መሥራት፤ በሌላ በኩል የሀገራችንን ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚያስከብር ዲፕሎማሲ በማጠናከር በዜጎች ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መተግበር እንዲሁም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የመሠረተ ልማትና የኢኮኖሚ ትስስር በመፍጠርና የገጽታ ግንባታ ሥራ በመሥራት የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ፤ ከጎሮቤት ሀገሮች ጋር የባህል ትስስሮችንና ጉድኝቶችን መፍጠር፤ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን በመመስረት እና በማጠናከር የሀገራችንን ገፅታ መገንባትና ተጠቃሚነታችንን ማረጋገጥ፤ የዳያስፖራውን የልማት ተሳትፎ ማሳደግ፤ የውጭ ኢንቨስትመንት በማሳደግ የውጪ ምርቶቻችን በዓለም አቀፍ ገበያ ያላቸውን ተደራሽነት ማስፋት እና የቱሪዝምን ፍሰት በማሳደግና የልማት አጋሮቻችንን በማበራከት እንዲሁም ዕውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታችንን ማሳደግ የሚሉት የዕቅዱ ዋና ዋና አላማዎች ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የሠላም ግንባታ እና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የሀገር ውስጥ ዘላቂ ሰላም መገንባት፤
    - የዜጋውን የውስጥ ሰላም የጥልቀት ዕድገት ከ25 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማድረስ፣
    - የዴሞክራሲ ተቋማት በሰላም ባህል ግንባታ ንቁ ተሳትፎ ዕድገት ከ5 ወደ 85 በመቶ ማድረስ፣
    - በማህበረሰብ ምክክር ማህበረሰባዊ ምክንያታዊነት፣ መግባባት፣ ችግር ፈቺነትና እርካታን ከ40 ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣
    - በልሂቅ-ተኮር ምክክርም የልሂቃንን ምክንያታዊነት፣ ጥምረት፣ የህዝብ አገልጋይነትና የዲሞክራሲ ተገዢነት ከ10 ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፤

- የህግ የበላይነትን ማስከበርና የደህንነት ተቋማት የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፤
    - በማህበረሰቡ፣ በፖሊስና በጸጥታ ተቋማት መካከል መተማመንን ከ40 ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣
    - የህግ አስከባሪ እና የደህንነት ተቋማትን አቅም ከ10 ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፤

- የማህበረ-ኢኮኖሚ ልማት እና የመቋቋም አቅምን ከ50 ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፤
- በክልሎች እና በፌደራል አስተዳደሮች መካከል የመተማመንና የመግባባት ደረጃ እና ክልል ለክልል ግንኙነትንና መተማመንን ከ25 ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፤
- አደረጃጀቶችን በትስስርና በትብብር በማጠናከር ሰላማዊነትንና አብሮነትን ከ40 ወደ 80 በመቶ ማድረስ፤
- አደጋን የመከላከልና የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ በተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ለተጎዱ ዜጎች ምላሽ የመስጠት ቅልጥፍናን ከ50 ወደ 95 በመቶ ማድረስ፤
- በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም፣ የተሻለ ማህበራዊ መስተጋብር፣ የኢኮኖሚ ትስስርና የጋራ ብልጽግናን በማጠናከር የአገራችንን ጥቅም ማስጠበቅ፤ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ሁሉን-አቀፍ ትብብር ተግባራዊ ማድረግ፤
- ከነባር ስትራቴጂያዊ አጋሮቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከርና አዳዲስ ስትራቴጂያዊ አጋሮችን በማፍራት

ለሰላማችንና ለልማታችን ፋይዳ ያለው ድጋፍ ማስገኘት፤

- ከተለያዩ ሀገሮች ጋር ያሉንን የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ማጠናከር፤
- አዳዲስ ግንኙነቶችን በመመስረትና የውክልና አድማሳችንን በማስፋት ለሰላማችንና ለልማታችን ድጋፍ ማስገኘት፤
- በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁ 300 ዋና ዋና ተፅዕኖ ፈጣሪ ተቋማትና 100 በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ላይ ከሚጽፉ ታዋቂ ግለሰቦች ጋር በመተባበር የገፅታ ግንባታ ስራ መስራት፤
- 50 የተመረጡ ዋና ዋና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሚድያዎች በሀገራችን ጉብኝት እንዲያደርጉ በማድረግ የሀገራችንን በጎ ገጽታ እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፤
- ከፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ጋር በመስራት የተመሰረቱ 225 ነባር ጉድኝቶችን ወደ 624 ማሳደግ፤
- የሀገራችን ከተሞችና ተቋማት ከሌሎች ሀገራት ጋር ትስስርና ጉድኝነትን እንዲፈጥሩ መደገፍ፤
- ለሥራ መዳረሻነት ከተለዩ ሀገራት ውስጥ 90 በመቶ ከሚሆኑት ጋር የሁለትዮሽ የውጭ የሥራ ስምሪት ስምምነቶች አዘጋጅቶ በመፈራረም ለ6 ሚሊዮን ዜጎች የውጭ የሥራ ዕድል መፍተር፤
- የዲያስፖራውን ማህበረሰብ በሀገር ቤት በተለያዩ ዘርፎች ማሳተፍ፤
    - 7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሀብት እንዲያፈሩ ማድረግ፣
    - ለ100,000 ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ማድረግ፣
    - በሀገር ውስጥ 148,000 የውጭ ምንዛሪ የባንክ አካውንት በማስከፈት የህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዥ እንዲፈጽሙ ማድረግ፣
    - ለዲያስፖራ ትረስት ፈንድ ድጋፍ የሚሰጡ አባላትን ቁጥር ወደ 400,000 ማድረስ።

# ምዕራፍ አስር

## የአስር ዓመቱ የአካባቢ እና
## የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዕቅድ

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች የሀገራችንን የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሃ-ሕይወት ሀብትን በማልማት፣ በማንበር፣ በመጠበቅ እና ዘላቂ አጠቃቀምን በማስፈን እንዲሁም ጤናማ የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብርን በማሳደግ ዘላቂ ሀገራዊ ልማትና እድገት እንዲረጋገጥ ማድረግ ናቸው።

የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዋና ዋና ዓላማዎች በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የመጤ ወራሪ ዝርያዎችን መለየትና እያደረሱ ያሉትን ጉዳት በጥናትና ምርምር በመታገዝ በቅደም ተከተል መቅረፍ፤ የተለያዩ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን በመሰብሰብ የጀኔቲክስ ሀብትን ማንበር፤ ከዘርፎች የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መጠን መቀነስ እና የደን፣ የብዝሀ ህይወትና የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃን ማጠናከር ናቸው።

የቀጣዩን አስር ዓመታት (2013-2022) የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል።

- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት አሁን ካለበት 92.7 ሚሊዮን ቶን ካርቦንዳይኦክሳይድ እኩሌታ (MtCO-2eq.) ወደ 162.3 ሚ.ቶን ካርቦንዳይኦክሳይድ እኩሌታ መቀነስ፤
- በዱር እንስሳት መጠለያ የሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶችን የመከላከል ሽፋን ከ62 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፤
- ሀገራዊ የደን ሽፋንን ከ15.5 በመቶ ወደ 30 በመቶ ማሳደግ እና የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ከ8.6 በመቶ የቆዳ ሽፋን ወደ 14 በመቶ ማድረስ፤
- የዱር እንስሳትና የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን የማበልጸግ ስራን ከ311,470 በ2022 ወደ 743,447 ማሳደግ፤ የማንበር ሥራን ከ179,285 ዝርያዎች ወደ 764,361 ዝርያዎች ማሳደግ፤

# ምዕራፍ
# አስር አንድ

## የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ
## የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች
## እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

# 11.1 የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ሊደረስባቸው የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚሆኑ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ሥልቶች በእያንዳንዱ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ውስጥ በዝርዝር ተመላክተዋል። በዚህ መሠረት የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች በጥቅሉ እንደሚከተለው ቀርበዋል። በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ጥራት ያለውና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እና ወደ አስተማማኝ የዕድገትና የብልጽግና ጎዳና ለመሸጋገር ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በአንድ ሀገር ውስጥ የሚመዘገብ አነስተኛ የካፒታል ክምችት ከአነስተኛ ቁጠባና ኢንቨስትመንት የሚመነጭ ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ትርጉም ያለው የልማት ፋይናንስ በማመንጨት ከብክነት በፀዳ መልኩና በቅልጥፍና ለታለመለት ዓላማ በማዋል ጥራት ያለው ዕድገት ማስመዝገብና የካፒታል ክምችትን ማሳደግ ይቻላል።

በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ዋና ዋና ግቦችን ዕውን ለማድረግ የልማት ፋይናንስ አቅርቦት እና ፍላጎት ማዕቀፍን (Resource envelope) በግልጽና በዝርዝር ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የልማት ፋይናንስ ምንጭን ከሀገር ውስጥ ገቢና ቁጠባ እንዲሁም ከውጭ ምንጮች በአግባቡ በመለየት፣ የኢኮኖሚውን ገቢ የማመንጨት አቅም ከግምት በማስገባት፣ የልማት ዕቅዱ ባስቀመጣቸው የትኩረት መስኮችና አቅጣጫዎች ቅደም ተከተል መሠረት ቅልጥፍናና ውጤታማነትን ባገናዘበ መልኩ አቅርቦትን እና ፍላጎትን በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የተቀመጠውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማሳካት የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠንና ዝርዝር የልማት ፋይናንስ ምንጭ የሚያሳይ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል።

በዕቅዱ የትግበራ ዘመን የመንግሥት በኢንቨስትመንት ወጪ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ዋና ዋኖቹን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግቦች ለማሳካት በሚያስችሉ ከፍተኛ ምርታማነት ባላቸው ዘርፎች ላይ በማተኮር የመንግሥት ኢንቨስትመንት ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል። እንዲሁም ጥራት ያለው የመንግሥት ኢንቨስትመንት በማከናወን በዕቅዱ የተመለከቱትን ግቦች በተለይም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስመዝገብ፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከማስፈን፤ ድህነትን ከመቀነስ፤ የግል ዘርፉን ድርሻ ከማሳደግ፤ የሀገሪቱን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ከማዋል፣ ዘርፎች መካከል ትስስር እና ተመጋጋቢነት በማጎልበት የሥራ ዕድል ከመፍጠር እና የወጪ ንግድን ከማሳደግ አንጻር  የኢንቨስትመንቱን ቅደም ተከተል የሚመሩ መሠረታዊ መነሻዎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

ለዚህም በመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር 1210/2012 ዓ/ም መሠረት በዕቅዱ ዘመን በመንግሥት የሚከናወኑ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶችን በሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዝርዝር ጥናት ላይ ተመስርተው በጥልቀት እንዲዘጋጁ ይደረጋል። ፕሮጀክቶቹም በገለልተኛ ወገን ተገምግመው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አዋጭነታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ ይደረጋሉ። በተጨማሪም በዕቅዱ ዘመን የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነትና ቅልጥፍና ለማሳደግ ከላይ በተጠቀሱ መስፈርቶች መሠረት በየዘርፉ የተለዩትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል። በተመሳሳይ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ተግባራዊ የሚደረጉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ለተቀመጠው የልማት ግብ የሚኖራቸውን ፋይዳ እንዲሁም የሚጠበቁ መስፈርቶችን ማሟላታቸው ተረጋግጦ ይተገበራሉ።

ጥራት ያለው የሰው ኃይል የኢኮኖሚን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማረጋገጥ በዕቅዱ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖረዋል። የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነትና በጥራት ማቅረብ ካልተቻለ የዕቅዱን ትላልቅ ግቦች ለማሳካት አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም ከኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አቅርቦትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነት፣ በጥራት እና በመጠን ከኢኮኖሚው ባህሪ ጋር ተለዋዋጭ በመሆኑ ይህንን ቀድሞ በማቀድ መዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም የትምህርት ዘርፉ የሚያቀርበው የሰው ኃይል ከኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚከሰተውን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን (skill mismatch) ከማስወገድ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ዘላቂ ምርታማነትን እውን በማድረግ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ያለው አዎንታዊ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የልማት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ፍላጎት በክህሎት አይነት፣ መጠንና የጥራት ደረጃ በየዘርፉ በዝርዝር የሚለይ የልማት ዕቅዱ የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

## 11.2 ክልላዊ እና አካባቢያዊ የተመጣጠነ ልማት እና ተወዳዳሪነት

ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የመንግሥት አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የተደረጉ የልማት ዕቅዶች ሀገራዊ የልማት ዕቅዱን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ቢሆንም ከሀገራዊ የልማት ዕቅዱ ጋር የሚያሥተሳሥራቸው የአሠራር ሥርዓት አልነበረም። በተጨማሪም በክልሎች እና ከክልሎች በታች ባሉ የመንግሥት አስተዳደር አካላት ደረጃ ጠንካራ የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ የትግበራ እና የአፈጻጸም ክትትል አቅም እንዲሁም በቂ ፋይናንስ አለመኖር በዕቅዶቹ ተግባራዊነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎችን እምቅ አቅም በመለየት እነዚህን አቅሞች መሠረት ያደረገ የተደራጀ የኢንቨስትመንት ፍሠት በታቀደ መልክ ባለመከናወኑ በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ የተፈጥሮ፣ የሰው ኃይል እና ሌሎች እምቅ አቅሞችን ስልታዊ በሆነ አግባብ ለመጠቀም አላስቻለም። በተጨማሪም በየደረጃው ያሉ በልማት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ሚና በግልፅ መግባባት የተደረሰበት ተቋማዊ እና ሕጋዊ አደረጃጀት እና የተሰጡ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችል የፋይናንስ ስልጣን እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አሰራር አልነበረም። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ ባሉ የመንግሥት አስተዳደሮች ከላይ ወደታች እና የጎንዮሽ ግንኙነት በሚጠበቀው ደረጃ ካለመኖሩም በላይ የትብብር ማዕቀፉ ደካማ ነበር። ይህም በፌዴራል፣ በክልል እና በወረዳ አስተዳደሮች ታቅደው ተግባራዊ የተደረጉ ኢንቨስትመንቶች ለሀገራዊ ልማት የሚኖራቸውን አስተዋጽዖ እና የሀገሪቱን ውስን ሀብት ውጤታማነት በአግባቡ እንዲያረጋግጥ አላደረገም። በተጨማሪም የክልሎች የልማት ዕቅድ የአጎራባች አካባቢዎችን እና የልማት ዘርፎችን በማቀናጀት እና በማስተሳሰር አለመከናወኑ የቅንጅት ችግር አስከትሏል።

ባለፉት ዓመታት በፌዴራል መንግሥት እና በተለያዩ የመንግሥት አካላት የተከናወኑ መሠረተ ልማቶች ፍትሐዊነትን እንዲያስፋፉ ከማድረግ አንጻር ሰፊ የሆነ ሥራ የተሰራ ቢሆንም በክልሎች እና ከክልሎች ከማዕከላት ርቀው በሚገኙ አካባቢዎች የመንገድ፣ የመብራት እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ፍትሐዊ ስርጭት ላይ ክፍተቶች ተስተውለዋል። በመንገድ መሠረተ ልማት ዘርፍ ወረዳዎችን ከፌዴራል መንገድ ጋር ከማገናኘት አንጻር በሀገሪቱ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የግብርና እና ሌሎች ተፈጥሮዊ እምቅ አቅሞች ያሉ ቢሆንም የመንገድ መሠረተ ልማት በአንፃራዊነት በእነዚህ አካባቢዎች

ባለመስፋፋቱ ያላቸው እምቅ አቅም ጥቅም ላይ እንዳይውል በማድረግ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንጻር ማነቆ ሆኗል። ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ በከተማና በገጠር መካከል ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድል ልዩነት በመፈጠሩ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት እንዲጨምር፣ በከተሞች እና በገጠር አካባቢዎች መካከል ያለው የመሠረተ ልማት አቅርቦት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ልዩነት ደግሞ አብዛኛውን ሕዝብ የተሻለ አገልግሎት ለማግኘት ከተሞችን እንዲመርጥ አድርጓል። የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች እንዲሁም ክልሎች ለወረዳዎች የበጀት ድጎማ በማድረግ ተመጣጣኝ የሆነ የፊስካል አቅም በመፍጠር የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በአገልግሎት ላይ ያለው የጥራት ደረጃ እና ተደራሽነት በክልሎች መካከል እንዲሁም በክልልሎች ውስጥ በገጠር እና በከተማ ወረዳዎች እና አካባቢዎች እንዲሁም ለማዕከል ቅርብ እና ሩቅ በሆኑ አካባቢዎች መካከል አለመመጣጠን ተፈጥሯል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተማ ልማትን ለማዘመን እና የከተማ አሰፋፈርን ለመምራት የሚያስችሉ መጠነ ሰፊ የሆኑ የጥናት ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ከተሞች ካላቸው ውስጣዊ ጥንካሬ አንጻር ያላቸውን አቅም ለመጠቀም የሚያስችል የከተማ አመራር አለመኖሩና ከተሞች እና በከተሞች ዙሪያ ያሉ አካባቢዎችን አቀናጅቶ ከማቀድ እና ከመምራት አንጻር የተሞከሩ ሥራዎች ውጤታማ አለመሆናቸው ከተሞች በሚያስፈልጋቸው መጠን ፋይናንስ በማሰባሰብ የመሠረተ ልማት እና የልማት ሥራዎች በማከናወን ከተሞችን በሚጠበቀው ደረጃ ለኑሮ ምቹ ማድረግ አልተቻለም። ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ከተሞችን እንደዋነኛ መዳረሻ እያደረገ ቢሆንም በከተሞች ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ እምብዛም በመሆኑ የሥራ አጥነት ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በተጨማሪም ሀገሪቱ የምትከተለው የከተማ አሰፋፈር አማራጭ በሁሉም አካላት መግባባት ተደርሶበት እየተተገበረ ባለመሆኑ በከተሞች ውስጥ የህገ ወጥ ግንባታዎች፣ የከተሞች ኢመደበኛ መለጠጦች (urban sprawl) እና የከተማ ውስጥ እና በከተማ ዙሪያ የመሠረተ ልማት እና የመንግሥት አገልግሎቶች እጥረቶች እንዲከሰቱ ምክያት ሆኗል።

በከተሞች ውስጥ የመሬት አጠቃቀም በዕቅድ ባለመመራቱ ከተሞች ወደ ግብርና እና ገጠር አካባቢዎች ባልታቀደ መልክ በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ። በከተሞች ላይ የተሠራው ሥራ እምብዛም ከመሆኑ አኳያ አዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ በዕቅድ ላይ ያልተመሠረተ እና የከተማዋን የወደፊት ዕድገት እና በሀገሪቱ የከተሞች የተመጣጠነ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መከማቸት እና ያልታቀደ የሰው አሰፋፈር እያታየ ይገኛል። በክልል ዋና ዋና የከተማ ማዕከሎች እና በአዲስ አበባ የሚታዩ ተግዳራቶች በተመሳሳይ ሁኔታ መታየት የጀመሩ ሲሆን እነዚህን ተግዳሮቶች በተቀናጀ መልክ የማስተዳደር እና የመፍታት እንቅስቃሴ በተደራጀ ሁኔታ የተመራ ባለመሆኑ ችግሩ እየተባባሰ ይገኛል። በአርብቶ አደሩና ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ሥነ-ምኅዳሩን መሠረት ያደረገ የልማት ሥራ አለማከናወን፣ የህብረተሰቡን ምርትና ምርታመነት የሚያሳድጉ የግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም ችግር፣ የመጠጥ ውኃ እና የእንስሳት መኖ እጥረት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የግጦሽ መሬት መመናመን፣ የመሠረተ ልማት ሽፋን አነስተኛ መሆን፣ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቃም ግጭቶች መኖር፣ የእንስሳት ገበያ ትስስር ዝቅተኛ መሆን፣ የአየር ንብረት ለውጥና ድርቅ፣ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚከናወኑ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች በጥናትና በቅንጅት አለማከናወንና የአርብቶ አደር አካባቢ ልማትን የሚመራ የማስፈጸሚያ ፖሊሲ አለመኖር ተጠቃሽ ማነቆዎች ናቸው።

በአጠቃላይ እነዚህ የክልላዊ እና የአካባቢያዊ የልማት ሥራዎች የተከናወኑት በየደረጃው ባለው ሕጋዊ የመንግሥት አደረጃጀት በኩል (administrative regional planning approach) ሲሆን በተቀናጀ መንገድ ቦታን (space) መሠረት በማድረግ በተደራጀ ሁኔታ በአካባቢያዊ የልማት ዕቅድ ማዕቀፍ (spatial planning framework) የተከናወኑ አልነበሩም። በመሆኑም በቀጣይ የአስር

ዓመታት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ያሉትን እምቅ የተፈጥሮ አቅሞች መሠረት ያደረገ የኢንቨስትመንት ፍሰት እና የመሠረተ ልማት ስርጭት እንዲኖር የማድረግ፤ ክልሎች እና የአካባቢ መስተዳድሮች ተጨባጭ ሁኔታቸውን መሠረት አድርገው ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ከማድረግ ባሻገር እነዚህ የልማት ዕቅዶች ሀገራዊ የልማት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የክልላዊ፣ አካባቢያዊ እና የተመጣጠነ ልማት ማዕቀፍን መሠረት ያደረገ የልማት ዕቅድ እንዲኖር ይደረጋል። በተጨማሪም የተፈጥሮ ሀብት እምቅ አቅምን ለመጠቀም እና ፍትሐዊና ውጤታማ የመሠረተ ልማት አገልግሎት ሥርጭትን እና ተጠቃሚነትን እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የአካባቢ ጥበቃን ለማከናወን የሕዝብ አሰፋፈርን በታቀደ ሁኔታ የመምራት፤ የተለያዩ አካባቢዎችን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ለማዋል በቅድሚያ መሠረተ ልማቶችን የማልማት እና የልማት ቀጠናዎችን ለማልማት የፋይናንስ አቅርቦትና የማትጊያ አስተዳደራዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል።

በተጨማሪ በሀገራዊ የልማት ግቦች ላይ በየደረጃው ስምምነት ላይ በመድረስ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዘርፎች እና አካባቢዎች ማዕከል ያደረገ የኢንቨስትመንት ክንውን እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሕግ ከተቀመጠው የአስተዳደረዊ እርከን በተጨማሪ በተለያዩ ደረጃ ያሉ የልማት ሃይሎች በትብብር የልማት ሥራዎችን ማከናወን አለባቸው። በሀገሪቱ የትኛውም አካባቢ የሚኖር ዜጋ ተመጣጣኝ የሆነ የመንግሥት አገልግሎት እና መሠረተ ልማት እንዲያገኝ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እና እምቅ አቅም ለመጠቀም የሚያስችሉ አካባቢዎችን በልዩ ትኩረት ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ ባሻገር የተለያዩ ክልሎች እና የሀገሪቱ አካባቢዎች ያላቸው እምቅ አቅም እና አለኝታ የተለያዩ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እነዚህ ቦታዎች ውጤታማ በሚሆኑበት ዘርፍ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ (specialization based on comparative and competitive advantage) በክልሎች እና በአካባቢዎች መካከል መስተጋብር እንዲኖር በማድረግ የልማት ትስስርን ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

ትላልቅ ከተሞችን በዙሪያቸው ካሉ ከተሞች ጋር በማስተሳሰር ማልማት (poly centric development)፤ በተመሳሳይ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ከተሞችን (secondary cities) ሚና በማሳደግ የሚገባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ፤ ትላልቅ ከተሞች ያላቸውን የተከማቸ የምርት፣ የሰው ኃብት እና የመሠረተ ልማት አቅም (agglomeration economies) በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ እና ኢንዱስትሪ መስፋፋቶች ወደሌሎች ውጤታማ ቦታዎች እንዲሰራጩ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰው ኃይል እና ኢንቨስትመንት ስርጭትን ውጤታማነት ለማጎልበት የዜጎችን በነፃነት መዘዋወር (Free Mobility) የሚያሳልጡ የሕግ ማዕቀፎችን፣ አሠራሮችን እና ማበረታቻዎችን መተግበር ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የኢንደስትሪን፣ የመሠረተ ልማትን እና የግብርና ልማትን ከመሬት አጠቃቀም ጋር በማስተሳሰር የተፈጥሮን ሁኔታ በመጠበቅ ልማት የሚበረታታባቸው (ሰፊ የከተማ ማስፋፋት እና ኢንደስትራላይዜሽን)፣ ልማት በታቀደ ሁኔታ የሚከናወንባቸው (ከተማ እና ኢንደስትሪ በተመጠነ ሁኔታ የሚስፋፉባቸው)፣ ልማት በተወሰነ ሁኔታ ብቻ የሚከናወንባቸው (የምግብ እና የአግሮ ኢኮሎጂካል ዞኖች) እና የማይፈቀዱ የመሬት አጠቃቀምን (የቅርስ እና የተፈጥሮ መስህቦችን) ማዕከል ያደረገ ልማት በማከናወን ዝቅተኛ አቅም ካላቸው አካባቢዎች ከፍተኛ አቅም ወዳላቸው አካባቢዎች እንቅስቃሴን እና አሰፋፈርን ማበረታታትና እነዚህን የሚያሳልጡ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ ማትጊያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

በተመሳሳይ የአርብቶ አደሩን የእንስሳት ሀብት በላቀ ደረጃ ለማልማትና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ ጥራት ያለው የእንስሳት ጤና ሽፋንና አገልግሎትን ማሳደግ፣ የእንስሳት ዝርያዎችን መጠበቅና ማሻሻል፣ የአርብቶ አደር አካባቢ ምርምርን ማሻሻል፣ የእንሰሳት መኖና ግጦሽ ልማትን ማስፋፋት፣ የገበያና ግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ እና በእያንዳንዱ እንስሳ ዓይነት የኤክስቴንሽን ፓኬጆችን መቅረፅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ከአርብቶ አደሩ በቅርብ ርቀት ከሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች ጋር በአጠቃላይ ልማት፣ በአገልግሎት፣በግብዓት እና ምርት አቅርቦት እንዲተሳሰሩ እንዲሁም የተለየ የኢኮኖሚ መሠረት ካላቸው አጎራባች አካባቢዎች ጋር በገበያ ትስስር እና በሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲተሳሰሩ መደረግ አለበት። የአርብቶ አደር እና የጠረፍ አካባቢዎች መሠረታዊ የሆኑ የአገልግሎት አሰጣጥን እና የመሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሻሻል ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖራትን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ትስስር በማጠናከር ለተያዘው የልማት ግብ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 11.3 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የአገራዊ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ዋና ዓላማ በየጊዜው የሚታቀዱ የልማት ዕቅዶችን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በመከታተልና በመገምገም ውጤታማ ሆነው እንዲፈጸሙ ማድረግ ነው። የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መከታተልና መገምገም በየጊዜው የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በፍጥነት ለመለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል። በዚህ ረገድ በሀገር ደረጃ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች እንደታየው ባለፉት የዕቅድ ዘመናት ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የክትትልና ግምገማ አሰራር በሀገሪቱ ለተመዘገበው ልማት የራሱ አስተዋፅኦ ቢኖረውም በርካታ ድክመቶችም ነበሩበት። ከድክመቶች መካከል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ቅንጅት ደካማ መሆን፣ በተለያዩ ደረጃዎች የክትትልና ግምገማ አቅም ውስን መሆን፣ በክትትልና ግምገማ ዙሪያ የተዛባ አመለካከት መኖር፣ የክትትልና ግምገማ አሠራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣ ከስኬት (outcome) ይልቅ ሂደትና ውጤት (process and output) ላይ ማተኮር እንዲሁም በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልፅነትና ተጠያቂነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ውጤታማ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩበት ግልፅና መለካት የሚችሉ ቁልፍ አመልካቾች (key performance indicators) ያስፈልጉታል። ይሄንንም ለማሳካት የፕላንና ልማት ኮሚሽን ከሁሉም አስፈፃሚ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል የራሱን ዘርፍ ቁልፍ አመልካቾች እንዲለይ በማድረግ አገራዊ ቁልፍ የውጤት አመልካቾች አዘጋጅቷል። በመሆኑም የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩት በእነዚህ አመልካቾች መሠረት ይሆናል።

ሌላው የክትትልና ግምገማ ዘዴ በዕቅድ ዘመኑ አጋማሽ ላይ የሚደረግ ግምገማ ነው። ዓላማውም በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ግቦች እና የማስፈፀም ኢላማዎች ምን ያህል እየተሳኩ እንደሆነ በዝርዝር ለመፈተሽና ለማረጋገጥ፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎች ካሉም በአስተማማኝ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድና በቀሪው የዕቅድ ዘመን የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንዲረዳ ነው። በመሆኑም የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ ይከናወናል።

የዕቅድ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ላይ የሚከናወን ግምገማ ሲሆን ዓላማውም የልማት ዕቅዱ ግቦች እና ኢላማዎች በዕቅዱ በተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎች እና የማስፈጸሚያ ሥልቶች መሠረት መፈጸማቸውንና የዕቅዱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ፣ መልካም ተሞክሮዎች እና የአፈጻጸም ጉድለቶች ካሉ ከነምክንያቶቻቸው በመለየት በቂ ትንተና እና ግምገማ ማካሄድ እና በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ ነው።

ሌላው የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ዘዴ በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የግምገማ ጥናት ማካሄድ ሲሆን በተመረጡ የማክሮ ኢኮኖሚ ወይም በዘርፎች የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እና ስኬቶች እንዲሁም ተግዳሮቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የግምገማ ጥናቶች ዓላማም በየጊዜው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ርዕሰ-ጉዳዮችን በመለየትና ቅደም-ተከተል በማውጣት ጥናቶችን በማካሄድ እየተመዘገበ ያለውን ለውጥ፤ ውጤትና የግብ ስኬት እንዲሁም እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥልቀት በመዳሰስ ለፖሊሲ ውሳኔዎችና ለዕቅድ ዝግጅት የሚረዱ መረጃዎችን ማመንጨት ነው።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን